ኢትዮጵያ : ዛሬ : በምትከታተለው : ፖለቲካዋና : በጂዮግራፊ : አቀማመጥዋ : የተነሣ : በምታደርገው : በማንኛውም : እድገታዊ : መንገድ : ከዛሬው : ዓለም : ጋር : ተካፋይ : መሆን : ግዴታ : አለባት ።

የአቶሚክ : ሳይንስ : መሻሻል : ለመላው : ዓለም : አዲስ : ዘመን : ከፍቶለታል ። በልዩ : ልዩ : የሳይንስ : ዘርፍ : ምርመራዎችም : በኩል : የአቶም : ኃይል : ከሁለቱ : ጉዳይ : ለአንደኛው : ለሰላም : ሲውል : ጠቃሚ : እንደሚሆን : አይጠረጠርም ።

ኢትዮጵያ : በየብስና : በአየር : ትራንስፖርት : ደግሞ : ከሌሎቹ : አገሮች : ጋር : ተወዳዳሪነት : ባለው : አስተዳደር : እንዳደረገችው : ከፍ : ያለ : እርምጃ : እንደዚሁም : ሙሉ : ተስፋ : በተጣለበት : በአቶሚካዊ : እድገት : ተካፋይ : ሆና : በአፍሪካ : ውስጥ : አሉ : ከሚባሉት : የመጀመሪያውን : ደረጃ : ከያዙት : አገሮች : አንደኛዋ : ለመሆን : ተስፋዋን : ማጠንከር : አለባት ።

በዚሁም : መሠረት : ለእርሻና : ለሕክምና : ለፊዚክና : ለባዮሎጅም : ምርመራ : ጠቃሚ : የሆኑ : የራዲዮ : አክቲቭ : አይዞቶፕስ : የሚጠኑባቸው : መሣሪያዎች : በቅርብ : ጊዜ : ውስጥ : እንዲዘጋጁ : ለማድረግ : አስበንበታል ።

ለጊዜው : የእኛ : ፈንታ : የግላችን : የሆነውን : የተፈጥሮ : ሀብት : ተመራምሮ : ማግኘት : ሕዝባችንም : እንዲጠቀምበት : ማድረግና : በተቻለ : መጠን : ከሌላው : ሕዝብ : ጋር : መካፈል : ስለሆነ : የሳይንስ : ምርመራ : ሐሳብ : ደጋፊ : መሆን : ስላለብን : የአቶሚክን : ጉዳይ : ትምህርት : በታሪክ : ማጥናት : በዚህ : ተማሪ : ቤት : እንዲጀመር : ከተደረገ : ይኸው : ፫ : ዓመት : ሆኖአል ።

በኢትዮጵያ : አካባቢ : በሚገኙት : አገሮች : ጠቃሚ : የሆኑ : ምልክቶች : በማግኘታቸው : በኢትዮጵያም : ሊገኝ : ይቻላል : ብለን : ስለምናምን : ዩሬንያምና : እሱንም : የመሳሰሉት : የተፈጥሮ : ሀብት : የሚገኝበት : ምርመራና : ጥናት : ማድረግ : ተጀምሮአል ።

ይህም : ጥናት : በንጉሠ : ነገሥት : መንግሥት : ግዛታችን : እንዲደረግ : ፈቃደኛነታችንን : ስንገልጽ : የእግዚአብሔር : ፈቃዱ : ሆኖ : ውጤቱ : ፍሬን : ያዘለና : የተቃና : ከሆነ : ይህ : ዩኒቨርሲቲ : ኮሌጅ : የሚያ



ፈራቸው : አዋቂዎችና : ቴክኒሲያኖች : ችሎታቸውን : በሙሉ : የአቶም : ኃይል : ለሰላም : እንዲውል : ለማድረግ : የሚጥሩ : ወጣቶች : እንደምናገኝ : ከታላቅ : ተስፋ : ጋር : እንተማመናለን ።

ስለዚህ : በዩኒቨርሲቲ : ኮሌጅ : "የኒዩክሊየር" ወይም : የአቶሚክ : ፊዚክ : ትምህርት : በተጨማሪ : እንዲሰጥ : ፈቃዳችን : መሆኑን : ከአስተማሪዎቹ : የበላይ : ለሆኑት : ለዶክተር : ማት : ነግረናቸዋል ።

በሌሎች : አገሮች : ለሚደረገው : « ለጅዮፊዚክ » ሥራ : እርዳታችንን : እናደርጋለን ። ቍጥራቸው : ከአርባ : የሚበልጡ : አገሮች : ያሉበት : አንድ : የኅብረት : ድርጅት : መኖሩ : የታወቀ : ነው ። ይህም : ድርጅት : መሬት : « በጂዮማግኔቲክ » በኩል : ያላትን : ባሕርይ : ለመመርመር : የታቀደ : ነው ።

እንደ : ኤውሮፓ : አቆጣጠር : ከ፲፱፻፶፯ : እስከ : ፲፱፻፶፰ : ዓመተ : ምሕረት : መላው : ዓለም : ኢትዮጵያም : ጭምር : ለዚሁ : ድርጅት : አስፈላጊ : ሆኖ : የሚገኘውን : ጥናት : ለማድረግ : ይሰበሰባሉ ። ይህንኑም : ለመገንዘብና : መግባባትም : እንዲኖር : ለማድረግ : በመላው : ምድር : ማስተዋልና : መመራመር : አስፈላጊ : ነው ።

የኢንተርናሽናል : « ጂዮማግኔቲንግ » ማኅበር : ባቀረበው : ጥያቄ : መሠረት : መንግሥታችን : በዚሁ : በዓለም : በታወቀው : ድርጅት : ውስጥ : ተካፋይነቱን : ተቀብሏል ።

የአዲስ : አበባ : ዩንቨርሲቲ : ኮሌጅ : ደንበኛ : ሆኖ : ሙሉ : መሣሪያ : ያለው : «የጂዮማግኔተ.ንክ» መመርመሪያ : እንዲቋቋም : የፈቀድነው : ስለዚህ : ነው ።

የአዲስ : አበባ : አቀማመጥ : ጂዮማግኔቲክ : በሆነው : በምድር : አካፋይ : ስለሆነ : በዚህ : መሣሪያ : ረዳትነት : የሚደረገው : ምርመራ : ውጤት : ለእኛና : ለቀሩትም : አገሮች : የሚሰጠው : ጥቅም : ታላቅ : ነው ።

አገራችን : ሙሉ : እድገት : የሚኖራት : ከላይ : በተጠቀሰው : የሳይንስ : ክፍል : አዋቂዎችን : በማግኘት : ብቻ : ሳይሆን : በሌላም : ረገድ : ተገቢ : የሆኑና : ችሎታ : ያላቸውን : ሰዎች : በማሠልጠን : ነው ።

እስካሁን : ድረስ : በትምህርት : በኩል : በተደረገው : ጥረት : በቅርብ : ጊዜ : ውስጥ : ተደቅኖ : ለሚቆያቸው : ኃላፊነት : ዝግጁ : የሆኑ :

ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ወጣቶች ፡ ለማየት ፡ በመቻላችን ፡ ዛሬ ፡ የድካማችንን፡ ዋጋ ፡ አግኝተናል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ኢትዮጵያ ፡ እንደሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ በገንዘብ ፡ በአድሚኒ ስትራሺን ፡ በተለይም ፡ በሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ በኩል ፡ እንደዚሁም ፡ አስተማሪ ፡ ከሌለ ፡ ተማሪ ፡ አይገኝምና ፡ መምህራንን ፡ በማሠልጠን ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ አለበት ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ችግር ፡ በመገንዘብ ፡ ወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ ሥራው ፡ እንዲከናወን ፡ መጣር ፡ ያለበት ፡ የትምህርቱን ፡ ብዛትና ፡ የራሱንም ፡ የወ ደፊት ፡ ዕድል ፡ መቃናት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሰውነቱን ፡ በሙሉ ፡ ለአገሩ ፡ በመሠዋት ፡ ነው ።

ወሮታ ፡ መላሽነቱንና ፡ የአገሩን ፡ ፍቅር ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያንነ ቱንም ፡ የሚገልጽበት ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ጭምር ፡ ከኤሌሜንታሪ ፡ ጀምሮ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማር ፡ የሰ ጠነውን ፡ ምክርና ፡ ትእዛዝ ፡ በብርቱ ፡ ትጋት ፡ ለመፈጸም ፡ መጣጣር ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባሩና ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

የእስያ ፡ ሕዝቦች ፡ በትምህርት ፡ የደረሱበትን ፡ ደረጃ ፡ ልናስበው ፡ ይገባናል ።

ታሪክና ፡ ትምህርት ፡ የጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ምንጮች ፡ ስለሆኑ ፡ ማናቸ ውም ፡ በትምህርት ፡ የጐለመሰና ፡ የበሰለ ፡ ሕዝብ ፡ የአገሩን ፡ ዕድል ፡ የሚጠቅም ፡ ጐዳና ፡ ሊመራ ፡ ይችላል ፡ የትምህርት ፡ እድገት ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ሳቢና ፡ መሪ ፡ ነው ።

እስካሁን ፡ በአገራችን ፡ የተደረገውን ፡ የትምህርት ፡ እድገት ፡ ካለ ፈው ፡ ዘመን ፡ ጋር ፡ ስናመዛዝነው ፡ አገሪቱን ፡ የሠላሳና ፡ የዓርባ ፡ ዓመት፡ እርምጃ ፡ አራምዷታል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። አሁንም ፡ ሕዝባችንን ፡ በቴ ዎሪ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ በገ ቢርም ፡ ጠቃሚና ፡ ተጠቃሚ ፡ ሆኖአል ።

በየጊዜው ፡ አንዳንድ ፡ ነቀፌታ ፡ እንሰማለን ፡ ይኸውም ፡ ነቀፌታ ፡ ሥራን ፡ በሥራ ፡ ለመመርመር ፡ የሚረዳ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ከዋናው ፡ መስመር ፡ የሚያፈናቅል ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።



ከምናስባቸውና ፡ ከምንደክምባቸው ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ የሕዝባችን ፡ ኑሮ ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ ስለሆነ ፡ የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒ ስቴር ፡ እንዲቋቋም ፡ አድርገናል ። የዚህም ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ ዜጎቻችን ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ የሚያድጉበትን ፡ ይልቁንም ፡ በተፈጥሮ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ መስፋፋት ፡ ምቹነት ፡ በሌላቸው ፡ ክፍለ ፡ ሀገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረው ፡ ዘላኑ ፡ ሕዝባችን ፡ በትምህርትና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ስብከት ፡ እየተመራ ፡ ትዳሩን ፡ ለማሻሻል ፡ በእርሻና ፡ በሌላም ፡ ዓይነት ፡ ሞያ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ማደራጀት ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ድርጅት ፡ ለመጠ ቀም ፡ ሕዝባችን ፡ የጉዳዩ ፡ ተቀባይና ፡ ተባባሪ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

የዚህ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ካመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ እየተቃና ፡ እንዲሄድ ፡ ለደከሙትና ፡ የሥራቸውን ፡ ፍሬ ፡ በያመ ቱ ፡ ለሚያሳዩን ፡ መምህራን ፡ በተለይም ፡ ለባለሥልጣኖቹ ፡ ቦርድ ፡ አባ ሎችና ፡ ለኮሌጁ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ደስታችንን ፡ ልንገልጽላቸው ፡ እንወዳለን ።

# 559

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከኦጋዴን ፡ አውራጃ ፡ ከኤደገ ሌና ፡ ከሐበር ፡ አወል ፡ ጐሣዎች ፡ ተልከው ፡ የመጡትን ፡ ባላባቶችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብለው ፡ ሲያነ ጋግሩአቸው ፡ ከባላባቶቹ ፡ አንዱ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ/ ከባላባቶቹ ፡ ከአንዱ ፡ የተነገረው ፡ ቃል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በዛሬ ፡ ቀን ፡ እግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ለመቅረብ ፡ ዕድል ፡ ያገኘነው ፡ ታማኝ ፡ ዜጎችዎ ፡ በኦጋዴን ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ በአዋሬ ፡ አካባቢ ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ሆነው ፡ በሚገኙ ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ በሚቆጠሩ ፡ የኢደገሌ ፡ ጐሣዎች ፡ ተመርጠን ፡ ጉዳታችንንና ፡ በደላችንን ፡ ከፍ ፡ ላሉት፡ መሪያችን ፡ ለማመልከት ፡ ልዩ ፡ መልክተኞች ፡ ሆነን ፡ የመጣን ፡ የዚሁ ፡ ጐሣ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሽኮዎች ፡ ነን ።

ይህ ፡ የኛ ፡ ጐሣ ፡ ሠፍሮ ፡ የሚገኘው ፡ የሣር ፡ ግጦሽ ፡ ክልል ፡ ተብ ሎ ፡ በሚጠራው ፡ መሬት ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ ከአዋሬ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ እን ግሊዝ ፡ ሶማሌላንድ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ በተነጠፈው ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነው ።

ይህም ፡ መሬት ፡ ከአባቶቻችን ፡ ከአያቶቻችን ፡ ከቅድም ፡ አያቶቻ
ችን ፡ ጀምሮ ፡ በጠቅላላም ፡ የጐሣችን ፡ ስምና ፡ ታሪክ ፡ ከተፈጠረበት ፡
ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የኖርንበት ፡ የትውልድ ፡ አገራችን ፡
ነው ።

በዚሁ ፡ በምንኖርበት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ የእንግሊዝ ፡ ላይዘን ፡
ኦፊሰሮችና ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ የጐሣ ፡ ድርጅት ፡ አባሎች ፡ የራሳ
ቸውን ፡ ጐሣና ፡ የዜጎቻቸውን ፡ ጉዳይ ፡ በማከናወን ፡ ፈንታ ፡ በኛ ፡ በኢት
ዮጵያውያኖቹ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ ሰላም ፡ በመንሣታቸው ፡ በኑሮአ
ችን ፡ የደረሰውን ፡ ችግር ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲያቃልልልን ፡ የታማኝ ፡ ዜጎ
ችዎን ፡ አቤቱታ ፡ ለማሰማት ፡ መጥተናል ።

ከእንዲህ ፡ ያለው ፡ በደልና ፡ ጥቃት ፡ እንድንጠበቅ ፡ በማሰብ ፡
ከ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሾሙልን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡
ለችግራችን ፡ የቅርብ ፡ ታዛቢዎች ፡ ሆነው ፡ በሚገባ ፡ ጠብቀው ፡ ያስተዳ
ድሩን ፡ ነበር ። ጠላት ፡ አገራችንን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወሩበት ፡ ጊዜም ፡ በደ
መወዝ ፡ ሲተዳደሩ ፡ የነበሩት ፡ ባላባቶቻችንና ፡ በወታደርነትም ፡ ተቀጥ
ረው ፡ ሲያገለግሉ ፡ የነበሩት ፡ የኤደገሌ ፡ ዜጎችዎ ፡ በየጦሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡
ሲከላከሉ ፡ በኢትዮጵያዊነታቸው ፡ የመከራው ፡ ተካፋዮች ፡ ሆነው ፡ ደማ
ቸውን ፡ ላገራቸው ፡ ያፈሰሱ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ስንተዳደር ፡ የቆየን ፡ ዜጎችዎ ፡ ጠላት ፡ አገራችንን ፡
ወርሮ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ መጀመሪያ ፡ በኢጣልያ ፡ ቀጥሎም ፡ በእንግሊዝ ፡
መንግሥት ፡ ይዞታ ፡ ምክንያት ፡ ግንኙነታችን ፡ ተቋርጦ ፡ በመጨረሻ ፡
የምንኖርበት ፡ አገር ፡ ለቀድሞ ፡ ባለቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ በማሕላችን ፡ ያለው ፡
ከለላ ፡ ስለተወገደ ፡ ዛሬ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለመገናኘት ፡ በመቻላችን ፡
እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግናለን ።

የሕዝባችን ፡ ኑሮና ፡ ሕይወት ፡ ከብት ፡ በማርባት ፡ ላይ ፡ የተመሠ
ረተ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የከብቶቻችንም ፡ ሕይወት ፡ በሣርና ፡ በውሃ ፡
ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ በመሆኑ ፡ ይህንን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠንን ፡ ሲሳይ ፡
በፀጥታና ፡ በሰላም ፡ ለመጠቀም ፡ እንድንችልበት ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ለሚ
ገኙ ፡ ዜጎችዎ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ለኛም ፡ መብታችን ፡ እንዲከበርና ፡
እንዲጠበቅ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንለምናለን ።



የአገራችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የኛ ፡
ክፍል ፡ የሆነው ፡ በሪዜርብድ ፡ ኤርያ ፡ ስም ፡ በእንግሊዝ ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡
በመቆየቱ ፡ እያዘንን ፡ ስንኖር ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ የነበረንን ፡
ነፃነታችንን ፡ አግኝተን ፡ በራሳችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መን
ግሥት ፡ በመተዳደራችን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀ
ርባለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ይህንን ፡ ያገኘነውን ፡ ነፃነት ፡
እንዲቀርና ፡ ስናዝንበት ፡ ወደ ፡ የነበረው ፡ አስተዳደር ፡ እንድንመለስ ፡ ከ
ውጭ ፡ የሚደረገውን ፡ ፕሮፓጋንድ ፡ በቃልም ፡ በሐርጌሳ ፡ ራዲዮ ፡ በየቀ
ኑ ፡ ሲሰበክ ፡ እየሰማን ፡ እናዝናለን ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮአች
ንን ፡ ለመንሳት ፡ የሚደከምበት ፡ መሆኑን ፡ ተረድተናል ።

በመብታችን ፡ መጓደልና ፡ በደረሰብንም ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ በደ
ሉን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለማሰማት ፡ አስበን ፡ ከቆየን ፡ ብዙ ፡ ወራቶች ፡ አል
ፈዋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ችግራችንን ፡ ለማመልከት ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ
ሥታችን ፡ ብንመጣ ፡ የእንግሊዝ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሐርጌሳ ፡ ራዲዮ ፡
ጣቢያ ፡ አማካይነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የእንግሊዝ ፡ ዜጎች ፡ የሆ
ኑትን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ደመወዝ ፡ ለመክፈልና ፡ ከውስጣቸውም ፡ ባላባት ፡
ለመሾም ፡ አባብሎ ፡ ወስዷቸዋል ፡ ብለው ፡ እኛን ፡ የነርሱ ፡ ዜጎች ፡ በማ
ስመሰል ፡ ያናገሩትን ፡ በመስማታችን ፡ በጣም ፡ ተገርመንበታል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ኢትዮጵያዊነታችን ፡ ሊፋቅ ፡ የማይቻለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚኖ
ረው ፡ መላው ፡ የኤደገሌ ፡ ሕዝብዎ ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡
የማይበገር ፡ መሆኑን ፡ እኛ ፡ መልክተኞቹ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከአዋሬ ፡ ኦንሥቶ ፡ እስከ ፡ እንግሊዝ ፡ ሶማሌላንድ ፡
ወሰን ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ እኛ ፡ በምንኖርበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በአስተዳደር ፡
ረገድ ፡ ጉዳታችንና ፡ ጥቅማችንን ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ የሚታዘቡልን ፡ እን
ደድሮው ፡ በሚያስፈልገው ፡ መጠን ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አስተ
ዳዳሪዎች ፡ ስለሌሉን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ሥር ፡ የምንተዳደ
ረው ፡ ዜጎችዎ ፡ ከባዕድ ፡ የተሰነዘረ ፡ የጉልበት ፡ ጥቃት ፡ እንዳያገኘን ፡

በኤደንገሌ ፡ ሕዝብዎ ፡ ስም ፡ ሆነን ፤

፭ኛ ፤ ጠቃሚ ፡ በሆኑ ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ የመንግሥቱ ፡ በቂ ፡ የጸጥታ ፡ አስከባሪዎች ፡ እንዲደረጉልን ፤

፮ኛ ፤ በሌላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ለሚኖሩት ፡ ሕዝቦችዎ ፡ እንደ ተደረገው ፡ ሁሉ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ሰፊ ፡ ችሮታ ፡ ለኛም ፡ ባላባቶች ፡ እን ዲሾሙልን ።

፯ኛ ፤ የምንኖርበት ፡ አገር ፡ የማር ፡ ምቾት ፡ ሲኖረው ፡ በበጋው ፡ ወራ ት ፡ ውሃ ፡ የለውም ፤ በዚህ ፡ ችግር ፡ የተነሣ ፡ ሕዝቡ ፡ ውሃ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሱማሌላንድ ፡ መሰደድ ፡ እንዳይደርስበት ፡ በአገ ራችን ፡ ባለንበት ፡ ስፍራ ፡ ውሃ ፡ ተቆፍሮ ፡ እንዲወጣ ፡ እርዳታ ፡ እንዲ ደረግልን ።

፰ኛ ፤ በውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ በኩል ፡ ያሉብንን ፡ አንዳንድ ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ሐረር ፡ ላይ ፡ ለክቡር ፡ ኰሎኔሎ ፡ ክፍሌ ፡ ያመለከትን ፡ ስለሆነ ፡ በርሳቸው ፡ በኩል ፡ ተመርምሮ ፡ የሚቻለው ፡ እንዲፈጸምልን ፡ እንለም ናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፤<br>
ዕድሜ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችዎ ፤<br>
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።<br>
የታማኝ ፡ ዜጎችዎ ፡ መልክተኞች ።

❊ ❊ ❊

ለ/ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የምታቀርቡትን ፡ አቤቱታና ፡ ችግራችሁን ፡ በየጊዜው ፡ ሰምተናል ። ከወዳጅ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ባደረግነው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ፀጥታ ችሁ ፡ እንዲከበርና ፡ የደረሰባችሁም ፡ ችግር ፡ እንዲወገድ ፡ እናደርጋለን ።

በማናቸውም ፡ እረገድ ፡ በወሰናችን ፡ ግቢ ፡ የሚገኙትን ፡ ኢትዮጵ ያዊ ፡ የሆኑ ፡ ዜጎቻችንን ፡ ሁሉ ፡ መጠበቅ ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባራችን ፡ ስለ ሆነ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ እናደርግላችኋለን ። በውሃውም ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ወደሌላ ፡ ግዛት ፡ ለመሄድ ፡ እንዳትገደዱ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሚበቃ ፡ ውሃ ፡ እንድታገኙ ፡ እናደርግላችኋለን ።



# 560

ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እሑድ ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ክቡር ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ገብረ ፡ መስቀ ል ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ተብለው ፡ የትግሬን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መንበረ ፡ ጵጵስና ፡ በመንበረ ፡ ፀባዖት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሾሙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተነገረ ፡ ቃል ።

ሀ/ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ንግግር ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አሜን ። እኵት፡እግዚአብሔር፡ዘዘልፈ፡የዐቀበነ፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከክሕደት ፡ ከኑፋቄ ፡ የ ሚጠብቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ከመፈጠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ነበረ ፤ ክቡ ር ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ ከዛሬም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፤ ሲከበር ፡ ሲመሰገን ፡ ሲሠለስ ፡ ሲቀደስ ፡ ይኖራል ፤ ይኑር ፡ አሜን ።

ግርማዊ ሆይ ።

እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ከፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ያለቸር ፡ ጠባቂ ፡ አልተዋትም ። አባቶችዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በተፈጥሮአ ቸው ፡ አእምሮ ፡ ጠባይ ፡ የተቃናላቸው ፡ ደጋጎች ፡ ስለሆኑ ፡ ሥጋዊንና ፡ መንፈሳዊውን ፡ አመራር ፡ አመዛዝነው ፡ ሲመሩት ፡ እንደኖሩ ፡ ታሪክ ፡ ይነ ግረናል ። እንዲያውም ፡ እናትዎ ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ አንድ ፡ ነቢይ ፡ አንድ፡ ካህን ፡ ሳያስተምራት ፡ በራሷ ፡ ሐሳብ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዳ ፡ ሃይማኖተ ፡ አ ራትን ፡ ማምጣቷንና ፡ ኋላም ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ልከው፡ ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መዘርጋታቸውን ፡ ስናመዛዝን፡ ከሥጋዊ ፡ ለመንፈሳዊው ፡ ያደላሉ ፡ ብንል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ከዐረብ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ እያስተ ረጎሙ ፡ ያመጡልን ፡ ነገሥታት ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ከኢትዮጵያዊቱ ፡ ንግሥት ፡ ማክዳና ፡ ከይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ከሰሎሞን ፡ የተወ ለዶ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከወለዳቸው ፡ ነገሥታት ፤ ሕገ ፡ መንግሥትንና ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አድርጎ ፡ አመዛዝኖ ፡ ከማስተዳደ ር ፡ በቀር ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ቸል ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ አይገኝም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቢሆን ፡ የክህነቱ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ተ ወላጅ ፡ ያውም ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ የተጨበጠ ፡ በመሆኑ ፤ በቋ

ንቋ ፡ መለያየትና ፡ በሀገር ፡ ርኅቀት ፡ ከመቸገሯ ፡ በላይ ፡ ያው ፡ አንዱ ፡ ጳጳስ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ መንበረ ፡ ጵጵስና ፡ እየተራቆተ ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ማለፋቸውን ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ይነግሩናል ።

ይህንንም ፡ በመገንዘብ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳትን ፡ እያሾሙ ፡ ራሷን ፡ ለማስቻል ፡ የደከሙ ፡ ነገሥታት ፡ ብዙዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ሳይፈጸምላቸው ፡ አለፉ ።

ይህ ፡ ሐሳባቸው ፡ እውነተኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሐሳብ ፡ ሲሆን ፡ ሳይፈጸም ፡ መቈየቱ ፤ ይህ ፡ ዕድል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የተጠበቀና ፡ የደለበ ፡ ሀብት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

እግዚአብሔር ፡ የፈቀደበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ግን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ አስነሣ ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ብዙ ፡ አባቶች ፡ በተምኔት ፡ ያሳለፉት ፡ ተስፋ ፡ ተፈጸመ ። የዚህም ፡ የተስፋ ፡ አፈጻጸም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ምኞት ፡ ላለመሆኑ ፡ በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለዚህ ፡ ማዕርግ ፡ ተቀዳሚዎች ፡ ሆነው ፡ የተሾሙ ፡ አባቶቻችን ፡ ያሳዩት ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኗል ።

ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ በፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተመሠረተው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መንፈሳዊ ፡ ትግል ፡ ለዚህ ፡ ማዕርግ ፡ ከበቃሁ ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤ ተቀብተው ፡ ሲሾሙ ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ የጳጳሳቱም ፡ ቍጥር ፡ ዘጠኝ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በጠቅላላውም ፡ በግብጽ ፡ ፓትርያርክ ፡ ተቀብለው ፡ ከተሾሙት ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፲፩ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚገኙባት ፡ ሀገር ፡ ሆናለች ። በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሾሙት ፡ ጳጳሳትም ፡ እንደየሀብታቸው ፡ በጎ ፡ ሥራቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ስላለፉና ፡ ሌሎች ፡ ስለተተኩ ፡ ዛሬ ፡ ያሉት ፡ ጳጳሳት ፡ ሁለተኛ ፡ ትውልድ ፡ ናቸው ፡ ሊባል ፡ ተችሏል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በውነቱ ፡ እኒህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርናቸውንና ፡ ሌሎቹንም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትጋት ፡ ተጀምረው ፡ ከፍጻሜ ፡ የደረሱትን ፡ ተግባሮች ፡ በዓይነ ፡ ልቡና ፡ ስንመለከታቸው ፡ አባትዎ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ "በረሲዓን ፡ ምክር ፡ ያልሄደ ፡ በኃጥአን ፡ ጐዳና ፡ ያልቆመ ፡ በዋዘኞች ፡ ሸንጎ ፡ ያልተቀመጠ ፡ ፈቃዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ በመዓልትም ፡ በሌ



ሊትም ፡ ሕጉን ፡ የሚመለከት ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያሰበውን ፡ ያደርጋል ፡ የተመኘውን ፡ ያገኛል ፡ የጀመረውን ፡ ይጨርሳል" ብሎ ፡ የተናገረ ፡ ስለግርማዊነትዎ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ስንናገር ፡ የእውነተኝነት ፡ ደስታ ፡ ስሜት ፡ ይሰማናል ።

ከዚህም ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ዳር ፡ ተተከላ ፡ ቅጠሏ ፡ ሳይረግፍ ፡ ቅጠል ፡ ፍሬዋ ፡ ሳይረግፍ ፡ ፍሬ ፡ እንደምትሰጥ ፡ ዛፍ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ የተነገረው ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘር ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡ አሜን ።

❋ ❋ ❋

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ የሚገባትን ፡ ክብር ፡ እንድታገኝ ፡ የደከምንላት ፡ ዓላማ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ ለማየት ፡ ላበቃን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ።

በኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እጅ ፡ የተፈጸመውን ፡ የጵጵስና ፡ ሢመት ፡ ስናይ ፡ ዛሬ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሆንዋል ። የክርስቲያን ፡ ደሴት ፡ በሆነች ፡ አገራችን ፡ ከአራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የተመሠረተችውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዘመኑ ፡ ማዕበል ፡ እንዳያናውጣት ፡ እናንተ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ወንጌልን ፡ ለመዘርጋትና ፡ የክርስቶስን ፡ መንግሥት ፡ ለማሳወቅ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ በበለጠ ፡ ልትደክሙበት ፡ የሚገባ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ በያዘ ፡ ቍጥር ፡ የሚኖረውም ፡ አላፊነትና ፡ አሳቢነት ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ መሆኑን ፡ ማሰብ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

በምትሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ደጋፊ ፡ እንዲሆናችሁ ፡ እንመኛለን ። እኛም ፡ እርዳታችንን ፡ አናጓድልባችሁም ።



ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ስለሆነ ፡ ከጠዋቱ ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

በቤተ ፡ መንግሥት ፡ መሳፍንትንና ፡ መኳንንትን ፡ እጅ ፡ ሲያሥነሡ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ የተነገረ ፡ የምርቃት ፡ ቃልና ፡ በ፳ ፡ ሰዓት ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በሰገነት ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ በታዩ ፡ ጊዜ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ከንቲባ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

ሀ/ በኢትዮጵያውያን ፡ ስም ፡ የተወከሉ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ የተናገሩት ፡ የምርቃት ፡ ቃል ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ ዘተሣሀለነ ፡ ወገብረ ፡ መድኀኒተ ፡ ለሕዝበ ፡ ዚአሁ ፡ አንሥአ ፡ ለነ ፡ ቀርነ ፡ መድኀኒትን ፡ እምቤተ ፡ ዳዊት ፡ ገብሩ ።

የኢትዮጵያ ፡ ብርሃን ፡ ግርማዊ ፡ ሆይ ።

መንበረ ፡ መንግሥትዎን ፡ አጽንተው ፡ ሀገርዎን ፡ አስፋፍተው ፡ ጠላትዎን ፡ አጥፍተው ፡ ታሪክዎን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ አስታውቀው ፡ ሕይወትዎን ፡ ጠብቀው ፡ ዘርዎን ፡ አለምልመው ፡ የአሰቡትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ በጠቅላላው ፡ ሥራዎን ፡ ባርኮና ፡ ቀድሶ ፡ ከዚህ ፡ ከስድሳ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ ለስድሳ ፡ አምስተኛው ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ የአደረሰዎ ፡ ቸሩ ፡ አምላካችን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ጃንሆይ ።

ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብዎ ፡ የሕይወት ፡ ዋስ ፡ የነፃነት ፡ ብርሃን ፡ የሥልጣኔ ፡ ፋና ፡ የጥበባት ፡ ሁሉ ፡ መፍለቂያ ፡ የሆነው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የተገኙበትን ፡ ይህን ፡ ዕድለኛ ፡ ቀን ፡ ለማክበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆነን ፡ በዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ የቆምነው ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

እኛ ፡ ብቻ ፡ ሳንሆን ፡ በዚህ ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ የማይለውና ፡ የዋሉለትን ፡ ታላቅ ፡ ውለታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያደረጉላትን ፡ ሙሉ ፡ አገልግሎት ፡ የማያስታውስ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አይገኝም ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ለሕይወትዎ ፡ የምንሳሳውና ፡ ዕድሜውን ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ መቆየት ፡ የምንመኘው ፡ ለራሳችን ፡ ስንል ፡ ነው ።

ያለግርማዊነትዎ ፡ ሕይወት ፡ ሌላ ፡ መድኀኒት ፡ እንደሌለን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታውቋል ፤ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከልብዎ ፡ ሳይሆን ፡ ከፊትዎ ፡ ብንርቅ ፡ በመከራ ፡ ማዕበል ፡ ተውጠን ፡ አይዟችሁ ፡ ብሎ ፡ የደረሰልን ፡ ማንም ፡



አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕይወትዎን ፡ ለሞት ፡ ምቾትዎን ፡ ለመንገላታት ፡ ለውጠው ፡ በውጭ ፡ አገርና ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ከባድ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሥቃይ ፡ ተቀብለው ፡ እንደ ፡ ትንቢት ፡ ተናግረው ፡ በሰጡት ፡ ቀጠሮ ፡ ልክ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ሲመለሱ ፡ የዋጠን ፡ ጨለማ ፡ ተገፈፈ ፡ የመከራችን ፡ ዘመን ፡ አለፈ ። በጭንቀ ፡ ሥፍራ ፡ ደስታ ፡ ተተካበት ። ደማችን ፡ በፈሰሰበት ፡ አደባባይ ፡ የነፃነት ፡ ብርሃን ፡ ሰፈፈበት ። በጠቅላላው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በጦርነትና ፡ በሰላማዊ ፡ ዘመን ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ባሳብ ፡ በሥራ ፡ በመራር ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝብዎ ፡ የደከሙት ፡ ድካምና ፡ የፈጸሙት ፡ ተአምራዊ ፡ ሥራ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ ሰፈውን ፡ ውለታዎን ፡ ያወቀልዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑ ፡ በየጊዜው ፡ በአደረገልዎ ፡ ቸርነትና ፡ በፈጸመልዎ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ሊታወቅ ፡ ችሏል ።

ፈጣሪያችን ፡ የተለመደውን ፡ ቸርነቱን ፡ ሳያጓድል ፡ ከሚወድዎትና ፡ ከሚወዱት ፡ ሕዝብዎ ፡ ጋር ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ሰጥቶ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲያኖርልን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡ የምታቀርበው ፡ ጸሎት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሁላችንም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡

ዕድሜ ፡ ለንጉሣውያን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በእድገት ፡ ላይ ፡ እድገት ፡ እየጨመረች ፡ ለዘለዓለም ፡ በነፃነት ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ/ የክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ከዕለታት ፡ ሁሉ ፡ የተቀደሰችውን ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ የልደትዎን ፡ ስድሳ ፡ አራተኛውን ፡ ዓመት ፡ አክብሮ ፡ ደስታውን ፡ ለመግለጽ ፡ በተሰበሰበው ፡ የመናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ አጭር ፡ ቃላት ፡ እንድናገር ፡ ይፈቀድልኝ ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ሕዝብዎና ፡ በራሴ ፡ ስም ፡ ለስድሳ ፡ አራተኛው ፡ የልደት ፡ በዓልዎ ፡ አድርሶ ፡ በዓሉን ፡ ለማክበር ፡ ላበቃን ፡ አምላክ ፡ ምስጋና ፡ እያቀረብኩ ፡ የማቱሳላን ፡ ዕድሜ ፡ እንዲያድልዎ ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምኞቴን ፡ አቀርባለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ መሪነት ፡ ከጓደኞችዋ ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ወደፊት ፡ የምትገሠግሠው ፡ ኢትዮጵያ ፡ እርምጃዋ ፡ እንደቀጠለ ፡ ነው ። የግርማዊነትዎ ፡ ድካምና ፡ ጥረት ፡ ዛሬ ፡ ላለነውና ፡ ለመጭውም ፡ ትውልድ ፡ መመኪና ፡ ኩራት ፡ ስለሆነ ፡ ታሪክ ፡ ተጎናጽፎት ፡ ይኖራል ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በውጥን ፡ ከነበሩት ፡ ሥራዎች ፡ የገፈርሳ ፡ ግድብና ፡ ማጣሪያ ፡ የውሃ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ አገልግሎቱን ፡ ጀምሮአል ፤ ምንም ፡ መሥመሮቹን ፡ በከፍተኛ ፡ ቧንቧ ፡ በመለወጥና ፡ በማሻሻል ፡ ከታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ባይቻልም ፡ ካለፈው ፡ ዓመት ፡ የውሃ ፡ ችግር ፡ ተቃሏል ። በሚመጣው ፡ ዓመት፡ችግሩን ፡ ፈጽሞ ፡ ለማስወገድ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ዛሬ ፡ በአፍሪካ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ኦፔራ ፡ ከሚቆጠሩት ፡ ለመወዳደር ፡ የሚችል ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ። ቲያትር ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ ካገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቲያትሮች ፡ ተርፎ ፡ በዝናው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አርቲስቶች ፡ እየመጡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታዎች ፡ በማሳየት ፡ የሕዝቡን ፡ አእምሮ ፡ ማጐልመስ ፡ ጀምረዋል ።

በዘመናዊ ፡ ዕቅድ ፡ የተጀመረው ፡ የአዲሱ ፡ ቄራ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ሥራ ፡ እንደሚጀመርበት ፡ ታምኗል ።

የአስፋ ፡ ወሰን ፤ የማርሻል ፡ ስመትስና ፡ ሩዝቬልት ፡ መንገድ ፡ መገናኛ ፡ አደባባይ ፡ ፍል ፡ ውሃ ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሆስፒታል ፡ ጀርባ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ኡራኤል ፡ የሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞአል ።

የኤደንን ፡ መንገድና ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ አደባባይ ፡ አስ



ፍቶ ፡ ለአንድ ፡ መቶ ፡ አምስት ፡ አውቶሞቢል ፡ መቆሚያ ፡ ሥፍራ ፡ ጋራ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ተቃርቧል ።

አዲሱ ፡ ከተማ ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ የችርቻሮ ፡ መደብ ፡ አዳዲስ ፡ አነስተኛ ፡ ሱቆች ፡ በመሠራት ፡ አቅዱ ፡ ተሻሽሏል ፡ የቀረውንም ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ለመቀጠል ፡ አቅደናል ።

ብዙ ፡ የጽዳት ፡ መኪናዎች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አሳዝዘን ፡ የከተማው ፡ ጽዳት ፡ አገልግሎት ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄዷል ።

እንደዚሁም ፡ ዘመናዊ ፡ የሆኑ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ መኪናዎች ፡ አስመጥተን ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ቅልጥፍና ፡ ይፈጽማሉ ።

የክብር ፡ ሬሳ ፡ መጓዣ ፡ ስምንት ፡ መኪናዎች ፡ ደርሰውልን ፡ በቀረበው ፡ ፕላን ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ይቀጥላሉ ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ትእዛዝ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚኒስቴር ፡ ክፍል ፡ ከሚከናወኑ ፡ ከብዙዎቹ ፡ ጥቂቱን ፡ ሳልጠቅስ ፡ አላልፍም ።

የአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ ሲገሠግሥ ፡ ከትውልድ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣው ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባሩ ፡ አብሮ ፡ እንዲደረጅ ፡ ማስፈለጉን ፡ በማሰብ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የመሠረቱን ፡ ድንጋይ ፡ የጣለው ፡ ከፍተኛ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኮሌጅ ፡ በመሠረት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ኢትዮጵያ ፡ በቴክኒካዊ ፡ ረገድ ፡ ራሷን ፡ እንድትችል ፡ ማድረግ ፡ ከትምህርት ፡ ፕሮግራምዎ ፡ አንዱ ፡ ስለሆነ ፡ የሕንፃዎች ፡ ሥራ ፡ ኮሌጁ ፡ ተፈጽሞ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የታደሉትን ፡ ወጣቶች ፡ ይቀበላል ።

የንግድ ፡ ትምህርት ፡ የጨረሱ ፡ ወጣቶች ፡ በተሰማሩበት ፡ ክፍል ፡ መልካም ፡ የሥራ ፡ ክንውን ፡ ስላሳዩ ፡ የበለጠውን ፡ በስለውና ፡ ደርጅተው ፡ ለማገልገል ፡ እንዲችሉ ፡ ከፍተኛው ፡ የንግድ ፡ ኮሌጅ ፡ ሲሠራ ፡ ይታያል ።

አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ አገልግሎት ፡ በኋላ፡ በሕመም ፡ ወይም ፡ በርጅና ፡ ምክንያት ፡ ሠርቶ ፡ መኖር ፡ ሲያቅተው ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቅ ፡ የጡረታ ፡ ደንብ ፡ እንዲዘጋጅለት ፡ ስላዘዙ ፡ የሠራተኛው ፡ መንፈስ ፡ የበለጠ ፡ ነቅቷል ።

ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ትውልድ ፡ ያልፋል ፡ በደግ ፡ ሥራው ፡ መልካም ፡ ስምን ፡ የወረሰ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። በግርማዊነትዎ ፡ ሥራና ፡ ድካም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብዎ ፡ የነፃነት ፡ መድን ፡ የመልካም ፡ አኗኗርና ፡ የብልጽግና ፡ ዘመን ፡ ስለሆነ ፡ ዓላማዎን ፡ በመከተል ፡ የድካምዎ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ያድለን ፡ ስል ፡ ንግግሬን ፡ አሳጥራለሁ ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ እቴጌ ፡

ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ልጆችዎና

ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡

ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

---

# 562

የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ ዦን ፡ ሶቫኘርጌ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ፡ም ፡ በ፭ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ/ የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆኜ ፡ እንዳገለግል ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ የሰጡኝን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤና ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የሹመት ፡ አባቴ ፡ የሰጡኝን ፡ የአደራ ፡ ደብዳቤ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዳገለግል ፡ የተሰጠኝ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ማዕርግ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ መሆኑንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚቀመጠው ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈጽመው ፡ ለሚገባው ፡ ተግባር ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ከባድ ፡ አላፊነት ፡ እንዳለበት ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ ዐውቀዋለሁ ።



ለዚህ ፡ ለተሰጠኝ ፡ ክብር ፡ ተገቢ ፡ መሆኔን ፡ ለማሳየት ፡ ለሚፈለግብኝ ፡ አላፊነት ፡ ሁሉ ፡ የማልከይ ፡ ለመሆኔ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሊመኩብኝ ፡ ይችላል ።

እንዳልነበረ ፡ ሆኖ ፡ በተለዋወጠው ፡ አገር ፡ ውስጥና ፡ ይኸውም ፡ አገር ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ገና ፡ ሚዛኑን ፡ ባላገኘንበት ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሣይና ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥታት ፡ የሚያዋሕደው ፡ ወዳጅነት ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ የልማትንና ፡ የርምጃን ፡ አቋቋም ፡ የሚመሠርት ፡ ነው ።

በጋራ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወግ ፡ የተሳሰሩት ፡ ሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ በየሰዓቱ ለሚገጥሟቸው ፡ አንዳንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮችን ፡ እየተረዳዱ ፡ ሲአልፋቸው ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ አንድነት ፡ የተመሠረተውን ፡ መብታቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ የተማመኑ ፡ መሆናቸው ፡ ተሰምቷል ። ይህም ፡ በማንኛውም ፡ የኋላ ፡ ሁኔታ ፡ ፊት ፡ የሚሻር ፡ አይደለም ፡ እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ አገሮቻችንን ፡ ሊያሳስቡዋቸው ፡ የሚችሉ ፡ ጉዳዮች ፡ የተማመኑ ፡ ጎረቤቶች ፡ በቅንነት ፡ መንፈስ ፡ በተሳሰረ ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ ተነሣሥተው ፡ በትኩስ ፡ ሊፈጽሙት ፡ ከሚችሉትና ፡ ሊፈጽሙትም ፡ ከሚገባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ጋር ፡ የተመሳሰሉ ፡ ናቸው ።

እኔም ፡ ያለኝን ፡ የሥራ ፡ ትጋትና ፡ ቅልጥፍና ፡ የማሳየው ፡ ከጥንትም ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ የወዳጅነት ፡ መተሣሠር ፡ ደጋግሞ ፡ በማጥበቅ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ፈረንሣይን ፡ ለማዋሐድ ፡ ነው ።

ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ለመምጣት ፡ ስነሣ ፡ በፈረንሣይ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በተደረገልኝ ፡ አቀባበል ፡ ላይ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የፓሪስን ፡ ከተማ ፡ ጐብኝተው ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ በጥሞና ፡ አጫወቱኝ ።

እሳቸውም ፡ የግርማዊነትዎን ፡ እንግድነት ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ደስታ ፡ እንደተቀበሉና ፡ መላውም ፡ የፈረንሣይ ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ነጋሢ ፡ ሲጐበኘው ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶት ፡ እንደነበረ ፡ ነግረውኛል ።

ለግርማዊነትዎ ፡ ጸጋ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልማትና ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ለሕዝቡ ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ ያላቸውን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽልዎ ፡ ክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አዝዘውኛል ።

* * *

ለ/ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

## ክቡር ፡ አምባሰደር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የፈረንሣይ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ በታወቁት ፡ ተቀዳሚዎ ፡ ምትክ ፡ ከክቡር ፡ የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ በደስታ ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ በፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረጉትን ፡ ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡ ክቡርነትዎ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ ገልጸዋቸዋል ። እንደዚሁም ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነትና ፡ መግባባት ፡ በመዋለል ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ዓለም ፡ እርጋታና ፡ ሚዛን ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚረዳ ፡ መሆኑን ፡ በማመን ፡ ከገለጹት ፡ ስሜት ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ የምንስማማበት ፡ ነው ።

በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ አንዳንድ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ችግሮች ፡ ቢኖሩም ፡ በሁለቱ ፡ መልካም ፡ ጎረቤቶች ፡ መካከል ፡ እንደተነሡ ፡ ጉዳዮች ፡ ተቆጥረው ፡ በመግባባት ፡ መንፈስ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የኛና ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እርዳታ ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እርግጠኛ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

ከክቡር ፡ የፈረንሣይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ይዘውልን ፡ ስለመጡት ፡ የወዳጅነት ፡ መልክት ፡ ምስጋናችንን ፡ እያቀረብን ፤ ፓሪስንና ፡ የፈረንሣዊን ፡ አገር ፡ በጐበኘንበት ፡ ጊዜ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ደስታ ፡ እንዳለን ፡ እንደገና ፡ እንዲገልጹላቸውና ፡ በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የምናቀርበውን ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታዎች ፡ ለፈረንሣዊ ፡ ሕዝብ ፡ ልማትና ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ ጥልቅ ፡ ምኞት ፡ እንዲያደርሱልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

563

በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ትምህርታቸውን ፡ የጨረሱ ፡ ፭፻፫ ፡ ወጣቶችና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በችሎታቸው ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ፭፻፪ ፡ ወጣቶች ፡ በድምሩ ፡ ፺፭ ፡ ተማሪዎች ፡ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡



ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዲሄዱ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ ሐምሌ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከግርማዊ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ/ የወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ትምህርትታችንን ፡ ጨርሰን ፡ ወደ ፡ ውጭ አገር ፡ በምንሄደው ፡ በ፳፫ታችን ፡ ስምና ፡ ከሌላውም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በሚሄዱት ፡ ጓደኞቻችን ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ ንግግር ፡ ለማድረግ ፡ ዕድል ፡ በማግኘቴ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ።

ኢትዮጵያ ፡ ከሠለጠኑት ፡ መንግሥታቶች ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ እንድትሆን ፡ ሕዝቡ ፡ በእውቀት ፡ እንዲጐለምስ ፡ የኑሮውም ፡ ደረጃ ፡ እንዲሻሻልና ፡ እንዲደረጅ ፡ ለማድረግ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በየጊዜው ፡ ከማሰብና ፡ ከመድከም ፡ ተወስኖ ፡ አያውቅም ። በተለይም ፡ ትምህርት ፡ እንዲስፋፋና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ እንዲችል ፡ በማድረግ ፡ በያውራጃው ፡ በየወረዳውና ፡ በየቀበሌው ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተከፍተውና ፡ የመሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ተቋቁሞ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁ ፡ ወጣቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ከትምህርት ፡ ገበታ ፡ ቀርበው ፡ ዕውቀትን ፡ ሲሳተፉ ፡ ይታያሉ ። ይህም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሕዝብዎን ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሚወዱትና ፡ እንደሚያስቡለት ፡ ያሳያል ።

ሕዝብዎ ፡ በግልና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ እንዲጐለምስ ፡ ለማድረግ ፡ አዲስ ፡ የሕዝብ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲቋቋም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ፈቅዶ ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ የመሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራምና ፡ የሕዝብ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ መዘጋጀት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በትምህርትና ፡ በኤኮኖሚ ፡ እንድትራመድ ፡ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ኑሮዋም ፡ እንድትዳብር ፡ የሚያደርጋት ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ኢትዮጵያ ፤ በትምህርት ፡ በርሻ ፡ በንግድና ፡ በኢንዱ

ስትሪ ፡ በሳይንስና ፡ በቴክኒክ ፡ ረገድ ፡ እንድትሻሻልና ፡ እንድታድግ ፡ እስካሁን ፡ ያደረጉትን ፡ ለወደፊትም ፡ ያቀዱትን ፡ ፕሮግራም ፡ ሲመለከቱት ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ መሪ ፡ ላገሩ ፡ እድገትና ፡ ልማት ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ሊሠራ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጥረት ፡ ያልታገደና ፡ ሙሉ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ አጉልቶ ፡ ያሳያል ።

ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፡ በርሻ ፡ በትምህርት ፡ በኤኮኖሚ ፡ በአስተዳደር ፡ በሕግና ፡ በሳይንስ ፡ በኩል ፡ የሚሠሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያስፈልጓታል ።

አገራችን ፡ ምንም ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብታም ፡ ብትሆን ፡ በቂ ፡ ሠራተኞች፡ ካልተገኙ ፡ ወደፊት ፡ ለምታደርገው ፡ እርምጃ ፡ ዕንቅፋት ፡ የሚገጥማት ፡ መሆኑን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ተገንዝበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እየተላኩ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ማድረግ ፡ ከጀመሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖታል ።

ዛሬ ፡ እኛም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ ሄደን ፡ ትምህርታችንን ፡ ሲፈቅዱልን ፡ ወደፊት ፡ አገራችንን ፡ ተመልሰን፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተባብረን ፡ በመሥራት ፡ አገራችንን ፡ መርዳትና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ ማገልገል ፡ ዋና ፡ ተግባራችን ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘበዋለን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከዚህ ፡ ከታቀደው ፡ ሕዝባዊ ፡ እድገት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነን ፡ ለዚህ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ በመታጨታችን ፡ ለግርማዊ ፡ አባታችን ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናችንን ፡ በትሕትና ፡ እናቀርባለን ።

* * *

ለ/ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ እንደተናገርነው ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ወደኋላ ፡ እንዳትቀር ፡ አስበንበታል ። ያሰብነውንም ፡ ምንም ፡ በሙሉ ፡ ተከናውኗል ፡ ለማለት ፡ ባይቻል ፡ ሥራው ፡ ተጀምሮ ፡ ይኸውና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ስትራመድ ፡ ይታያል ።



እኛም ፡ ላገራችን ፡ እርምጃ ፡ ያሰብነውን ፡ ግብ ፡ ለማሰናከል ፡ የመጣውን ፡ ጠላታችንን ፡ ተቃውመን ፡ ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ እናንተን ፡ ለማድረስ፡ ችለናል ። ያቀድነውም ፡ ሙሉ ፡ ፍጻሜ ፡ እንደሚያገኝ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

አገራችን ፡ በጥንት ፡ ታሪኳ ፡ ከማናቸውም ፡ አገር ፡ ያላነሰችና ፡ የማይሞት ፡ ታሪክ ፡ የያዘች ፡ አገር ፡ ናት ፡ የጥንት ፡ ወሰኗና ፡ የሥልጣኔም ፡ ደረጃዋ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ በታሪክ ፡ ታገኙታላችሁ ።

አገራችን ፡ የጥንት ፡ ታሪኳን ፡ ደረጃ ፡ እንዳትለቅ ፡ በዛሬው ፡ እርምጃችን ፡ ወደፊት ፡ መግፋት ፡ ያስፈልጋል ። ይህንንም ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ በመሥዋዕትነት ፡ መሥራት ፡ ያሻል ። ዛሬ ፡ መሠራት ፡ የሚገባቸው ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ጌታ ፡ በወንጌል ፡ መከሩ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አጫጆቹ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፡ ያለው ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ እንዳይደርስ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ መብዛት ፡ አለባቸው ። የልጅነት ፡ ጠባይ ፡ አያታላችሁ ። የዛሬ ፡ ልጅነታችሁን ፡ ትታችሁ ፡ የነገ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ነን፡ በሉ ። ለሀገራችሁና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታችሁ ፡ ብድር ፡ መላሽ ፡ ሁኑ ፡ በሰውነት ፡ እንድትጠነክሩ ፡ አስበን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ስናያችሁ ፡ ብዙ ፡ ጡንቻ ፡ የላችሁም ።

ይህም ፡ ላሰብነው ፡ ሥራ ፡ እንዳትውሉ ፡ አያደርጋችሁም ። ሥጋ ፡ ይፈርሳል ። መንፈስ ፡ ግን ፡ አይፈርስምና ፡ የመንፈስ ፡ ደካማ ፡ አትሁኑ ።

እኛ ፡ ሁላችንም ፡ ነገ ፡ ሟቾች ፡ ነን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለማትሞተዋ ፡ አገራችን ፡ ጠንክራችሁ ፡ ሥሩ ፡ የነገርናችሁን ፡ አትርሱ ። ቀናውን ፡ መንገድ፡ ተከትላችሁ ፡ እንድትሠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳችሁ ።

---

# 564

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነሐሴ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ድሬ ፡ ዳዋ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ የፖሊስ ፡ ማሰልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተገኝተው፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሰልፍ ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ለሠራዊቱ ፡ የሰጡት ፡ መሪ ፡ ቃልና ፡ ትእዛዝ ።

ፖሊስ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆነና ፡ ሥራውም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የፖሊስን ፡ ሠራዊት ፡ ሰልፍ ፡ በጐበኘንበት ፡ ጊዜያት ፡ እንደተናገርነው ፡ ታውቁታላችሁ ። የፖሊስ ፡ ሥራው፡

ብዙ ፡ ዝርዝር ፡ ቢኖረውም ፡ ዋናው ፡ የጸጥታ ፡ ዋስ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ወገኑን ፡ ማሰብ ፡ አለበት ። ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የምናስብለት ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ አይደለንም ፡ እናንተም ፡ ማሰብ ፡ አለባችሁ ። አሁንም ፡ የምትሄዱበት ፡ አውራጃ ፡ ታላቅ ፡ ሀገርና ፡ ታላቅ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ ስለሆነ ፡ ራሳችሁ ፡ የምትታመኑ ፡ መሆን ፡ አለባችሁ ።

ራሳችሁን ፡ ካላመናችሁ ፡ ግን ፡ የጸጥታውም ፡ ዋስ ፡ ትሆናላችሁ ፡ የተሰጣችሁንም ፡ አደራ ፡ ትጠብቃላችሁ ፡ ተብሎ ፡ እምነት ፡ ሊጣልባችሁ፡ ካለመቻሉም ፡ በላይ ፡ እኛንና ፡ ሕዝባችንን ፡ አሳፋሪ ፡ ትሆናላችሁ ። ሰውን ፡ ሥራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስሙ ፡ አያስከብረውም ።

ስለዚህ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጸጥታው ፡ ዋስ ፡ ፖሊስ ፡ መሆኑን ፡ አውቃችሁ ፡ በምትሄዱበት ፡ አገር ፡ አደራ ፡ ለተጣለባችሁ ፡ ሥራ ፡ ትጉህና ፡ ታዛዥ ፡ ጠንቃቃ ፡ ሆናችሁ ፡ መገኘት ፡ ይገባችኋል ።

የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ በየዕለቱ ፡ ተፈላጊና ፡ ተጠያቂነት ፡ ያለበት ፡ ስለሆነ ፡ ከእኛ ፡ የተቀበላችሁትን ፡ አደራ ፡ አክብራችሁ ፡ አስከብራችሁና ፡ ተከብራችሁ ፡ እንድትፈጽሙት ፡ በጥብቅ ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

---

## 565

ለትምህርት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚሄዱ ፡ ፰ ፡ ሴቶችና ፡ ፲፱ ፡ ወንዶች ፡ በድምሩ ፡ ፳፯ ፡ ተማሪዎች ፡ ነሐሴ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፬ ፡ ሰዓት ፡ በድሬ ፡ ዳዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ነጋ ፡ ፈንታ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ/ የወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

እኛ ፡ ዛሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ የቀረብን ፡ ወጣቶች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትዎ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ስናገለግል ፡ ቆይተን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሕዝብዎ ፡ በትምህርት ፡ እንዲጐለምስ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ የሚጥርበትን ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በምንሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ከዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ ግርማዊ ፡ አባታችንን ፡ ስንሰናበት ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።



ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ጥረት ፡ የሕዝብዎ ፡ ደኅንነት ፡ በትምህርት ፡ እንዲደገፍ ፡ ስለሆነ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መጥቶ ፡ በድሬ ፡ ዳዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስለሚገኙ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ አስጠርተው ፡ አባታዊ ፡ ምክርዎን ፡ በመስጠት ፡ ሲያሰናብቱን ፡ ለሕዝብዎ ፡ ትምህርት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚያስብ ፡ ይህ ፡ ጉልህ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ።

ግርማዊነትዎ ፡ ዘወትር ፡ ከአእምሮዎ ፡ ሳይለይ ፡ የሚደክምበት ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነ ፡ ዛሬ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕውቀትን ፡ ለመማር ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ተዘጋጅተናል ። ሥልጣኔና ፡ ትምህርት ፡ እጅግ ፡ በተስፋፋበት ፡ በዚህ ፡ በዛሬው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደንበኛ ፡ ተገቢ ፡ ቦታዋን ፡ ይዛ ፡ ሕዝቧ ፡ በትምህርት ፡ አድጎ ፡ መሬቷ ፡ በልጽጎ ፡ እንዲያይዎት ፡ ለኛ፡ ለልጆችዎ ፡ የሚሰጡን ፡ የምክርና ፡ የማነቃቂያ ፡ ንግግር ፡ በአእምሮአችን፡ ውስጥ ፡ ዘልቆ ፡ ገብቷል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ለዘመናዊው ፡ የሥልጣኔ ፡ ብርሃን ፡ አብቅቶናልና ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ስንሄድ ፡ ታሪክ ፡ በአድናቆት፡ የሚመለከተውን ፡ ስምዎን ፡ አስከብረን ፡ ውለታ ፡ መላሾች ፡ መሆን ፡ የምንችለው ፡ ለተሰጠን ፡ ተግባር ፡ ተገቢዎች ፡ ሆነን ፡ ስንገኝ ፡ መሆኑን ፡ ሁላችንም ፡ ተረድተነዋል ። አሁንም ፡ የምንሄድበት ፡ ምክንያት ፡ በተለይ ፡ ለአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስፈላጊዎችና ፡ ምርጦች ፡ የሆኑ ፡ ትምህርቶችን ፡ ተምረን ፡ ስንመለስ ፡ የአገሩን ፡ ሰርዶ ፡ በአገሩ ፡ በሬ ፡ እንደተባለው፡ ሁሉ ፡ የአገራችንን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ ጠብቀን ፡ የሚሰጠንን ፡ የሥራ ፡ አላፊነት ፡ ታማኞች ፡ ሆነን ፡ እንድንሠራ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እኛም ፡ የምንላክበትን ፡ ተግባር ፡ ፈጽመን ፡ የኢትዮጵያ ፡

ተገቢ ፡ አገልጋዮች ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ እሙኖች ፡ ወገናችንን ፡ አፍቃሪዎችና ፡ አክባሪዎች ፡ ለመሆን ፡ የምንበቃው ፡ የግርማዊነትዎን ፡ የአባትነት ፡ ምክር ፡ በመከተል ፡ ስለሆነ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አደራ ፡ እንዲያስፈጽመን ፡ እንመኛለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰቦችዎ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ/ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላልሰን ፡ እንደነገርናችሁ ፡ ትምህርት፡ ለአገር ፡ ዋና ፡ የተፈተነ ፡ መድኃኒት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ስንናገር ፡ የትምህርት ፡ ጥቅም ፡ በሰፊው ፡ ባልታወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እናንተም ፡ ይህንኑ ፡ ተረድታችሁ ፡ በተቋቋመላችሁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በትጋት ፡ ስለተማራችሁና ፡ ትምህርታችሁን ፡ ስለአስፋፋችሁ ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ተልካችሁ ፡ ይህንኑ ፡ የደከማችሁበትን ፡ ትምህርት ፡ እንድትቀጥሉ ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

በንግግራችሁ ፡ እንደገለጻችሁት ፡ እናንተ ፡ በራሳችሁ ፡ ፈርዳችሁታል ። በትምህርታችሁ ፡ ባትተጉና ፡ መልካም ፡ ስማችሁን ፡ ባትጠብቁ ፡ ለኛም ፡ ለሀገራችሁም ፡ አሳፋሪ ፡ ከመሆናችሁ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ትምህርታችሁ ፡ የደከምንላችሁን ፡ ሁሉ ፡ ዋጋቢስ ፡ ታደርጉታላችሁ ። መልካም ፡ ትምህርትና ፡ ዕውቀት ፡ ለማግኘት ፡ በብዙ ፡ መታገል ፡ ያስፈልጋል ። የልጅነት ፡ መንፈስ ፡ ሳያሸንፋችሁ ፡ የሄዳችሁበትን ፡ ጉዳይ ፡ በሚገባ ፡ አከናውናችሁ ፡ ተመልሳችሁ ፡ አገራችሁን ፡ እንድታገለግሏት ፡ አገራችሁ ፡ እናንተን ፡ የሚያስፈልጋት ፡ ሆኗል ።

ለራስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሰውም ፡ ለመትረፍ ፡ ተጣጣሩ ፡ ራስን ፡ ብቻ ፡ መመልከትና ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አለመትረፍ ፤ ይልቁንም ፡ ለተማረ ፡ ሰው ፡ ዋና ፡ ጥፋት ፡ ነውና ፡ የትምህርታችሁ ፡ ምርት ፡ በዝቶ ፡ ሰፊ ፡ ሆኖ ፡ ለሌላውም ፡ ተራፊ ፡ እንዲሆን ፡ እንድታስቡበት ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ፡



እግዚአብሔር ፡ በሥልጣኑ ፡ ሁላችሁንም ፡ ጠብቆ ፡ ከሄዳችሁበት ፡ በደኅና ፡ መልሶ ፡ አገራችሁን ፡ እንድትረዱ ፡ ያብቃችሁ ።

# 566

የሶቪየት ፡ ዩኒየን ፡ ሶሲያሊስት ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ቦሪስ ፡ ካራቫኤብ ፡ መስከረም ፡ ፱ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ዓ. ም በ፫ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤአቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የሶቪየት ፡ ዩኒየን ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊክ ፡ ክፍል ፡ ከሆነው ፡ ከሱፕሪም፡ ሶቪየት ፡ ፕሬዚዳም ፡ የሶቪየት ፡ አምባሳደር ፡ ሆኜ ፡ የተሾምኩበትን ፡ ደብ ዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ይሰማኛል ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው ፡ የሶቪየት ፡ ሌጋሲዮንና ፡ እንዲሁም ፡ በ ሞስኮ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሌጋሲዮን ፡ ወደ ፡ ኤምባሲነት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ፡ ማለት ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሶቪየት ፡ ዩኒዮን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ እንዲበረ ታ ፡ የፈጸሙት ፡ ተግባራቸው ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ ይህ ፡ የወዳጅነት ፡ መንፈ ስ ፡ የመላውን ፡ ዓለም ፡ ሰላምና ፡ እንዲሁም ፡ የሕዝቦችን ፡ ፀጥታ ፡ የሚያ ጐለምስ ፡ ሁናቴ ፡ ነው ።

ከሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ በሚያደርገው ፡ ግንኙነት ፡ የሶቪየት፡ ዩኒየን ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ የሰላምን ፡ ጐዳና ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ የሌ ሎችን ፡ መንግሥታት ፡ ሥልጣን ፡ የማክበርን ፡ ተግባር ፡ የመተባበርን ፡ ዘዴ ፡ የሌሎች ፡ አገሮችን ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ድንጋጌ ፡ ያለመቃወምን ፡ በሰላም ፡ መኖርን ፡ ዓላማ ፡ በማድረግ ፡ መንግሥታቱ ፡ ታላላቅም ፡ ታናና ሽም ፡ ቢሆኑ ፡ የመንግሥታቸው ፡ አመራር ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን የሰላምን ፡ ፋና ፡ እየተከታተለ ፡ ይኖራል ። በዚሁ ፡ ዓላማው ፡ በመመራት ፡ ለሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ የሶቪየት ፡ ዩንየን ፡ መንግሥት ፡ ከኢ ትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነት ፡ ቋሚ ፡ አድርጎ ፡ በመግባባትና ፡ በመ ተማመን ፡ መንፈስ ፡ በየጊዜው ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ይመኛል ።

የሶቪየት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደር ፡ ሁኜ፡ ስሾም ፡ ለወደፊት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሶቪየት ፡ ዩኒየን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ እንዲበረታ ፡ ለመሥራት ፡ የተዘጋጀሁ ፡ መሆኔን ፡ እንድገልጽ፡

ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምናለሁ ። ከሶቪየት ፡ መንግሥት ፡ በተሰጠኝ ፡ አደራ ፡ መሠረት ፡ ሥራየን ፡ በማካሂድበት ፡ ጊዜ ፡ በግርማዊነትዎና ፡ በመንግሥትዎ ፡ በኩል ፡ አስፈላጊውን ፡ እርዳታ ፡ እንደማይነሳኝ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

＊ ＊ ＊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የሶቪየት ፡ ዩኒየን ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፐብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የመጀመሪያው ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሁነው ፡ የተሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ፡ እያለን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ለሚገኘው ፡ ግንኙነት ፡ ታሪክ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ዓይነተኛ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ እውነተኛ ፡ በሆነ ፡ ወዳጅነት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ እየጠነከረና ፡ እየተስፋፋ ፡ በመሄዱ ፡ የሁለቱ ፡ መንግሥታት ፡ ሌጋሲዮኖች ፡ ወደ ፡ ኤምባሲነት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፡ ስናደርግ ፡ ይህ ፡ መልካም፡ አስተያየት ፡ ጠቃሚነቱ ፡ በ፪ቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ለሚገኘው ፡ ግንኙነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለዓለም ፡ ጉዳዮች ፡ ጭምር ፡ መሆኑንና ፡ እንደዚሁም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሶቪየት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፐብሊክ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ ወዳጅነት ፡ በበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ ያላቸውን ፡ ምኞት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ ግንኙነት ፡ በየዕለቱ ፡ እያቀራረቡ ፡ የሚሄዱት ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡ የመንግሥታትን ፡ መብት ፡ ማክበር ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ የውስጥ ፡ ጉዳይ ፡ አለመግባት ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ የዩኒየን ፡ ሶቪየት ፡ ሶሺያሊስት ፡ ሬፐብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ሰላማዊ ፡ የውጭ፡ ፖለቲካውን ፡ የሚመራው ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ባለማጥቃት ፡ በእኩልነት ፡ በጋራ ፡ ጥቅምና ፡ አብሮ ፡ በመኖር ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ክቡርነትዎ ፡ የገለጡትን ፡ ማረጋገጫ ፡ በደስታ ፡ ተገንዝበነዋል ።

በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ በበለጠ ፡ ለማጠንከርና ፡ ለማስፋፋት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የእኛና ፡ የ



መንግሥታችን ፡ እርዳታ ፡ ምንጊዜም ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ።

# 567

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለጐልድ ፡ ኮስት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ለክዋሜ ፡ ንክሩማ ፡ መስከረም ፡ ፱ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ዓ. ም ያሳለፉት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ቴሌግራምና ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ የመጣው ፡ መልስ ።

ሀ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተላከው ፡ ቴሌግራም ።

ቴሌግራም ።

ለክቡር ፡ ክዋሜ ፡ ንክሩማ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ አክራ ፡ ጐልድ ፡ ኰስት ።

ጋና(ጐልድ ፡ ኰስት)በሚመጣው ፡ መጋቢት ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ነፃነቷን፡ የምታገኝ ፡ መሆኗን ፡ ክቡርነትዎ ፡ በሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ስለሰማን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህንም ፡ ታሪካዊ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ክቡርነትዎን ፡ በጋና ፡ መንግሥት ፡ ውስጥም ፡ የሚገኙትን ፡ የሥራ ፡ ጓደኞችዎንና ፡ የጋናንም ፡ ሕዝብ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አላችሁ ፡ እያልን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ምኞታችንን ፡ እንገልጻለን ።

ቀ. ኃ. ሥ. ን. ነ.

መስከረም ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

＊ ＊ ＊

ለ) ከክቡር ፡ ክዋሜ ፡ ንክሩማ ፡ የመጣ ፡ መልስ ።

ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡

ጐልድ ፡ ኰስት ፡ ሙሉ ፡ ነፃነቷን ፡ የምታገኝበትን ፡ ቀን ፡ ምክንያት፡ በማድረግ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለላኩልን ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መግለጫና፡ የሰላምታ ፡ ቃል ፡ በጐልድ ፡ኰስት ፡ ሕዝብ ፡ ሽም ፡ ሆኜ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ክዋሜ ፡ ንክሩማ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ።

ጐልድ ፡ ኰስት ፡

መስከረም ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

---

## 568

በበጌ ፡ ምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሲማሩ ፡ የነበሩት ፡ ፲፫ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ተማሪዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ ወደ ፡ እሥራኤል ፡ እንዲሄዱ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ መስከረም ፡ ፲፫ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ዓ. ም በ፲ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ) የወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ የምንታይ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውዘባ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስንማር ፡ ቆይተን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እሥራኤል ፡ አገር ፡ ሄደን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ እንድንማር ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለፈቀደልን ፡ ከገናና ው ፡ ከዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ቀርበን ፡ ምስጋናችንን ፡ ስናቀርብ ፡ የሚሰማን ፡ ደስታ ፡ መጠን ፡ የለውም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ወደ ፡ ተባለው ፡ አገር ፡ ስንሄድ ፡ በአገራችን ፡ ያለውን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ከግቡ ፡ አድርሰን ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንደኛው ፡ የጥበብ ፡ ኃይል ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ በመሆኑ ፡ ይህን ፡ ተምረን ፡ አገራችንን ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ መደገፍ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ስለተሰማን ፡ ነው ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፤
ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተሰብ ፤
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በእጁ ፡ ሠርቶ ፡ ያልበላ ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሊጠቀም ፡



አይችልም ። ስለዚህ ፡ ተምራችሁ ፡ ስትመለሱ ፡ አገራችሁን ፡ እንድትረዱ ፡ እንመኛለን ።

---

## 569

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ዓ. ም በ፫ ሰዓት ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ በሐረር ፡ ሜዳ ፡ ተገኝተው ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተምረው ፡ የተወሰነላቸውን ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ለፈጸሙት ፡ ካዴቶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀትና ፡ የበራሪነት ፡ ክንፍ ፡ የማዕርግ ፡ እድገትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሽልማት ፡ ሲሰጡ ፡ ለወጣቶቹ ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ይህ ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሥራ ፡ እንዲገኝ ፡ የተደከመበት ፡ ነው ።

በተጠራበትም ፡ ስም ፡ እንዲውል ፡ ብዛቱም ፡ ኃይሉም ፡ እምኞታችን ባይደርስ ፡ ባለን ፡ ገንዘብ ፡ ተሠርቶ ፡ የሀብታችን ፡ ትንሽነት ፡ እቅዳችንን ፡ አዘገየው ፡ እንላለን ።

ተስፋ ፡ ሳንቆርጥ ፡ የምናስፋፋው ፡ ላገራችን ፡ ላየርም ፡ ለምድርም ፡ ለሚደረገው ፡ መቋቋም ፡ ዋና ፡ ምርኩዝ ፡ ነው ። የትምህርታችሁን ፡ እድገት ፡ ለማየት ፡ በያመቱ ፡ በመጣን ፡ ቊጥር ፡ ውጤቱን ፡ የምንመለከተው ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ምክኒያትና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በግል ፡ስንጐበኛችሁ ፡ የምንሰጣችሁ ፡ ምክር ፡ (መሪ ፡ ቃል) በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ለምትከታተሉት ፡ ትምህርት ፡ እድገትና ፡ ስፋት ፡ አጥብቀን ፡ የምናስብበት ፡ መሆኑን ፡ ሳያስገነዝባችሁ ፡ አልቀረም ። ኢትዮጵያ ፡ ለጊዜው ፡ የኢኮኖሚዋ ፡ አኳኋን ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ በልማቷ ፡ በእድገቷ ፡ በብርቱ ፡ ከምንፈልገው ፡ ለአስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲረዳን ፡ ከሚችለው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ በእኛ ፡ ችሎታ ፡ ሊገመትና ፡ ሊናቅ ፡ የማይችል ገንዘብ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረጋችን ፡ በአቪያስዮን ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ እምነት ፡ ስላለን ፡ ነው ።

የሰው ፡ ፍጻሜ ፡ በሰፊው ፡ መራመድ ፡ የጀመረው ፡ የመገናኛ ፡ ብልሃት ፡ ተበጅቶ ፡ የመቃራረብና ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ልምድ ፡ እየበረታ ፡ ከሄደ ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

አኤሮፕላን ፡ በኮሚኒኬሽን ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ እንዲገ

ኝ ፡ እተደረገበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ለመገናኛ ፡ ሲያገለግሉ ፡ የነበሩት ፡ ብልሃቶች ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ በጊዜው ፡ ውስጥ ፡ ፍጥነታቸውና ፡ ምቾታቸው፡ እያደገ ፡ ቢሄድ ፡ ከመሬት ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ ጋራ ፡ የተሳሰሩ ፡ ስለሆኑ ፡ በጕዞአቸው ፡ ላይ ፡ ላያሌ ፡ ዕንቅፋቶች ፡ የተጋለጡ ፡ ነበሩ ።

አኤሮፕላን ፡ ግን ፡ በመሬትም ፡ ላይ ፡ በተዘረጋ ፡ ጐዳና ፡ እንዲሁም ፡ በባሓር ፡ በሚጓዘው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ መሰናክል ፡ ሳያደናቅፈው ፡ ነፃ ፡ በሆነ ፡ አየር ፡ ውስጥ ፡ በመብረር ፡ ወደ ፡ አሰበበት ፡ መድረሻው ፡ በቀጥታ ፡ በአቋራጭ ፡ መስመር ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ሊጓዝ የሚችል ፡ ብልሃት ፡ መሆኑ ፡ ከመቸውም ፡ ይልቅ ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ለመቀራረብ ፡ የተመረጠ ፡ መገናኛ ፡ መሆኑን ፡ በየዕለቱ ፡ እያሳመነን ፡ ሄዷል ።

ሰው ፡ ሲፈጠር ፡ እንደየዕድሉ ፡ በአእምሮ ፡ ተመሥርቶ ፡ ለጥበብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ባለመማር ፡ ባለ ማየት ፡ ባለመስማት ፡ መሆኑ ፡ ይኸው ፡ ተገለጸ ። በትምህርት ፡ ለመቀዳደም ፡ መሥጋት ፡ ለሰው ፡ የፈጠረበት ፡ ነው ። ስንፍና ፡ ደካምነት ፡ መሪውን ፡ አለመርዳትና ፡ አለመከተል ፡ የተረገመ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ። ፈጣሪውን ፡ አድላዊ ፡ እንዳያሰኝ ፡ በተማሩትና ፡ ባልተማሩት ፡ ምስክር ፡ ተገኝቷል ። ቆዳና አካል ፡ ምንም ፡ አይደለ ፡ ልብስ ፡ ነው ። አሁን ፡ ያላችሁት ፡ የት ፡ ነበራችሁ ? ዛሬ ፡ የት ፡ ደርሳችኋል ? የዛሬ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ባሳብ ፡ እንኳን ፡ ለመቃጣት ፡ የማይቻል ፡ ሲመስል ፡ የነበረው ፡ ፍጥነት ፡ ይዞ ፡ ብዙ ፡ ወራትና ፡ ቀናት ፡ ይጠይቁ ፡ የነበሩትን ፡ ጉዞዎች ፡ አሳጥሮ ፡ በስዓት ፡ እንዲሠፍሩ ፡ በማድረጉ ፡ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ የበለጠ ፡ መተዋወቅ ፡ እንዲኖር ፡ ከመተዋወቅም ፡ የሚፈልቀው ፡ መግባባትና ፡ መወዳጀት ፡ እንዲደረጅ ፡ ያደረገው ፡ እርዳታ ፡ ሲገመት ፡ አቪያስዮን ፡ በዘመናችን ፡ ከተፈጠሩት ፡ ብዙ ፡ ጥበቦች ፡ ከፍተኛው ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ይኸንንም ፡ አሳብ ፡ ስንከታተለው ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያገራችን ፡ አየር ፡ በሚጠብቁት ፡ ወጣቶች ፡ የሚሠለጥኑበትን ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ መግባባትና ፡ መተባበር ፡ በአኤሮፕላን ፡ በኩል ፡ በሚፈጸመው ፡ ተግባር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክንፍ ፡ ከሌሎች ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ሲቪል ፡ አእሮፕላን ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ አብራ ፡ እንድትሰለፍ ፡ የሚረዳ



ት ፡ ወጣቶች ፡ የሚሰናዱበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጭምር ፡ ነው ።

የዛሬ ፡ አስር ፡ ዓመት ፡ ይኸንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስንከፍት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ ወደያዛችሁት ፡ ዕድሜ ፡ ስትደርሱ ፡ እንዲከናወን ፡ ካቀድናቸው ፡ አሳቦች ፡ አንደኛ ፡ ምኞታችን ፡ አሁን ፡ ከምትበሩባቸው ፡ የተሻለ ፡ አኤሮፕላኖች ፡ ይዛችሁ ፡ ማየት ፡ ነበር ። ይህ ፡ በልዩ ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸምልን ፡ በመቅረቱ ፡ ሳያሳዝነን ፡ አልቀረም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ በበኩላችሁ ፡ በዚህ ፡ ባለው ፡ ባሮጊው ፡ መኪና ፡ በመጠቀም ፡ እረገድ ፡ የደረሳችሁበት ፡ የቅልጥፍና ፡ ደረጃ ፡ እንደዚሁም ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ያሠለጠናቸው ፡ ቴክንሲያኖች ፡ ቍጥራቸው ፡ በርክቶ ፡ መታየት ፡ እምነታችንን ፡ የሚያጽናና ፡ በጀመርነው ፡ መንገድ ፡ እንድንገፋበት ፡ የሚያበረታታን ፡ ሁኗል ።

ቴክንሲያኖች ፡ በሰው ፡ ጥበብ ፡ ለተፈጠሩት ፡ መኪናዎች ፡ ሁሉ ፡ ህይወት ፡ ናቸው ። በቴክኒሲያኖች ፡ ላይ ፡ የሚጣለው ፡ እምነት ፡ መኪናዎች ፡ እንዲንቀሳቀሱ ፡ ከማድረጉ ፡ በላይ ፡ ከበራሪዎቹ ፡ ሕይወት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ በመሆኑ ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚሰጠው ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ይገባል ። መኪና ፡ በመኪና ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ። ለሕይወት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ መተኪያ ፡ የለውም ። የክፍሉን ፡ የአሥር ፡ ዓመት ፡ ታሪክ ፡ ስናነሣ ፡ ከተጀመረ ፡ ጀምሮ ፡ በሕይወት ፡ ሁነው ፡ ላሰብንበት ዓላማ ፡ ይደርሳሉ ፡ ብለን ፡ የጓጓንላቸው ፡ ወጣቶች ፡ ለተወሰነ ፡ ዕድሜ ፡ ግማሽ ፡ ሳይደርሱ ፡ በሞት ፡ ሲለዩ ፡ የማይረሳ ፡ ፀፀት ፡ አሳድሮብናል ። እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ወጣቶች ፡ ማጣት ፡ ጉዳቱ ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ወጣት ፡ ሕይወታቸውን ፡ የሠውት ፡ ያመኑበትን ፡ ግብ ፡ ሲከተሉ ፡ ስለሆነ ፡ በሥጋቸው ፡ በመካከላችን ፡ ቢታጡም ፡ ጀግንነታቸውንና ፡ ቆራጥነታቸውን ፡ ጠብቃችሁ ፡ ልታኖሩት ፡ የሚገባችሁ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ታሪክ ፡ የሚመሠረተው ፡ በመከራና ፡ በኀዘን ፡ ላይ ፡ ነው ። የነሱም ፡ መሥዋዕትነት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አኤሮፕላን ፡ ጽኑ ፡ መሠረት ፡ ስለሆነው ፡ ጀግንነታቸውና ፡ ቆራጥነታቸው ፡ ለናንተ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የሚያኰራ ፡ ተግባር ፡ ነው ። አሁን ፡ የተፈጸመው ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ የመቋቋሚያና ፡ የመጠንከሪያ ፡ ዘመን ፡ ሁኖ ፡ ተፈጽሟል ።

ከዛሬ ፡ ወዲያ ፡ የምትይዙት ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ለምትከተሉት ፡ ግብ ፡

ሙሉ ፡ የሚያደርጋችሁን ፡ የቴክኒክና ፡ የሞራል ፡ ኀይላችሁን ፡ የምታደ
ራጁበት ፡ ዘመን ፡ መሆን ፡ አለበት ።

በዚህም ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የደከሙበትና ፡ የዚህንም ፡ ሥራ፡
ውጤት ፡ ያሳዩን ፡ የስዊድን ፡ አስተማሪዎች ፡ ውለታ ፡ የሚረሳ ፡ አይደለም
ከልብ ፡ እናመሰግናችኋለን ። አሳባችን ፡ በሥራ ፡ እንዲፈጸም ፡ እምነታችን
በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ነው

# 570

የምዕራባዊ ፡ ጀርመን ፡ ፌዴሬሽን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ፡
ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ዶክተር ፡ ሐንስ ፡ ቢደር ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ . ም .
በ፰ ፡ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነ
ገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የጀርመን ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከግርማዊነትዎ ፡
ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆኜ ፡ እን
ድሠራ ፡ የተሾምኩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ የሚሰማኝ፡
ክብር ፡ ከፍ ያለ ፡ ነው ።

በኢትዮጵያና ፡ በጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ ፍቅ
ርና ፡ ግንኙነት ፡ ለማስፋፋት ፡ በማደርገው ፡ ጥረት ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡
ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆኜ ፡ እንዳገለገል
ኩት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ለወደፊቱ ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ የምቀጥል ፡ ነኝ ።

ላገርዎ ፡ ለወደፊት ፡ እርምጃ ፡ ሲሉ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ላከናወኑት ፡
ሥራ ፡ ማስረጃዎች ፡ ከተገኙ ፡ በኋላ ፡ እንዲሁም ፡ አሁን ፡ የዚህ ፡ ትውልድ
ወጣት ፡ የሆነችው ፡ አገርዎ ፡ በበለጠ ፡ እንድትሠለጥን ፡ ለማድረግ ፡ የግር
ማዊነትዎ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ሆኗል ።

ይህም ፡ የተቃናና ፡ ተስፋ ፡ የተጣለበት ፡ ሥራ ፡ በመግባባትና ፡
ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ አድናቆት ፡ ከጀርመን ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ አሳብን
አግኝቷል ። ይህም ፡ የጋራ ፡ እምነትና ፡ መግባባት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሁ



ለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ጸንቶ ፡ የቆየውን ፡ የኤኮኖሚክና ፡ የጥበብ ፡
ኅብረት ፡ ሥራ ፡ ከማዳበሩም ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ አገር ፡ እድገት ፡ ታማኝነትና ፡
ስለ ፡ አገር ፡ ፍቅር ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ አሳብ ፡ ተሳስረው ፡ በሚከታተሉት
በሁለቱ ፡ ወጣቶቻችን ፡ መካከል ፡ የበለጠ ፡ ወንድማማችነትን ፡ እንደሚፈ
ጥር ፡ ተረድቸዋለሁ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ እንደሚያውቀው ፡ የሁለታችን ፡
አገሮች ፡ ግንኙነት ፡ ለወዳጅነት ፡ ጭምር ፡ በመሆኑ ፡ ደኅና ፡ ምስክር ፡
የሚያሻውን ፡ ሥራ ፡ በሙሉ ፡ ጉልበቴ ፡ እንደማከናውን ፡ ሳረጋግጥልዎ ፡
ዕድለኛ ፡ ነኝ ።

የዘመናዊዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፈጣሪ ፡ የሆኑት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ላገርዎ ፡
ላደረጉት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድካም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡
በቆዩበት ፡ ጊዜ ፡ መላው ፡ የጀርመን ፡ ሕዝብ ፡ ምስክር ፡ ከመሆኑም ፡
በላይ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ አድናቆቱን ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ገልጿል ፡ ወደፊት ፡
ለማከናውነው ፡ ሥራ ፡ የግርማዊነትዎና ፡ የመንግሥትዎ ፡ እምነትና ፡
እርዳታ ፡ እንደማይጓደልብኝ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ለማለት ፡ እደፍራለሁ ።
ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚሠሩት ፡ ጀርመኖች ፡ ሁሉ ፡ ለተደረገላቸው ፡
መልካም ፡ አድራጎት ፡ ጥበቃ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ እን
ዳቀርብ ፡ ይፈቀድልኝ ።

ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እድገትና ፡ ልማት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መል
ካም ፡ ጤና ፡ ያላቸውን ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽ ፡ የጀርመን ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑ
ብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የላኩኝን ፡ መልክት ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ግርማዊነትዎን ፡
እለምናለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

## ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የጀርመን ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡
መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡
አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ የቶሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡
ይለናል ።

በኢትዮጵያና ፡ በጀርመን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ወደፊት ፡
እያደገ ፡ መሄድን ፡ በመገንዘብ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡
የዲፕሎማቲክ ፡ ሚሺን ፡ ወደ ፡ ኤምባሲነት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ ስን
ፈቅድ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ መሆኑን ፡ ያውቀዋል ። አገራችንን ፡ ደኅና ፡ አድ
ርገው ፡ የሚያውቁት ፡ ክቡርነትዎ ፡ የጀርመን ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡
መንግሥት ፡ የመጀመሪያው ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡ በተለይ ፡
ደስ ፡ ይለናል ።

ክቡርነትዎ ፡ በንግግርዎ ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ የገለጡትን ፡ አዲሱን ፡
ተግባርዎን ፡ ለመፈጸም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የእኛ ፡ የዘወትር ፡ እር
ዳታችን ፡ የሚኒስትሮቻችንና ፡ የሕዝባችንም ፡ መተባበር ፡ እንደማይጓደል
ብዎ ፡ ልናረጋግጥልዎ ፡ እንወዳለን ። ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡
በማድረግ ፡ ለክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሄስ ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እን
ዲገልጹልንና ፡ እንደዚሁም ፡ በክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ አማካይነት ፡ በቅ
ርቡ ፡ ጊዜ ፡ ለጐበኘነው ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ ላሳደረብን ፡ ለጀርመን ፡
ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምታችንን ፡ እንዲያደርሱ ፡ እንዲያደ
ርጉ ፡ እንጠይቅዎታለን ።

# 571

የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡
ሆነው ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የመጡት ፡ ክቡር ፡ ሰይድ ፡ ዩሱፍ ፡ ሙስተፋ ፡ ኤልቲናይ ፡ ጥቅምት ፡
፳ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ዓ. ም በ፰ ሰዓት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀ
ርቡ ፡ የተናገሩት ፤ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡሩ ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መን
ግሥት ፡ ዘመን ፡ የመጀመሪያው ፡ የሱዳን ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባ
ሳደር ፡ እንድሆን ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶኝ ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤዬን ፡ ለግርማ
ዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ በዚህች ፡ በዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ የተሰጠኝ ፡
መሆኔ ፡ ይሰማኛል ። ይህ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ለራሴና ፡ ለልጅ ፡ ልጆቼ ፡ ሁል፡



ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኩራት ፡ ይሆናል ።

በዚህ ፡ መሠረት ፡ የሐጂ ፡ ካሌድ ፡ ተወላጆች ፡ (እኔም ፡ እራሴ ፡
ጭምር ፡) ካሁን ፡ በፊት ፡ የሐጂ ፡ ካሌድ ፡ ልጅ ፡ የነበሩት ፡ መሐመድ ፡
ኦስማን ፡ የመጀመሪያው ፡ የሱዳን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡ ለሰሎሞን ፡ ቤተ፡
መንግሥት ፡ በታላቁ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ በመሾማቸው ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ኩራት ፡ እንደተሰማን ፡ ነው ።

እኔ ፡ በበኩሌ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት
መካከል ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የቆየውን ፡ መልካም ፡ ግንኙነት ፡ ለማበር
ታትና ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ
ውን ፡ ታሪካዊ ፡ ወዳጅነት ፡ ለማጠንከር ፡ በትሕትና ፡ እሠራለሁ ።

የአገሬ ፡ ሐሳብና ፡ አስተያየት ፡ ከሁሉም ፡ አገሮች ፡ መወዳጀት ፡
ሲሆን ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ መሆናችን ፡ ሲገመት ፡ ጎረቤቶቻችን ፡ የመጀ
መሪያው ፡ የወዳጅነት ፡ መደብ ፡ አላቸው ።

ይህ ፡ አላፊነቱ ፡ ብዙ ፡ በሆነበት ፡ ተግባሬ ፡ ላይ ፡ የግርማዊነትዎና ፡
የመንግሥትዎ ፡ እርዳታና ፡ ድጋፍ ፡ እንደማይነሳኝ ፡ ተስፋ ፡ እንዳለኝ ፡
ለመግለጽ ፡ ይፈቀድልኝ ።

ከፍተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሱዳን ፡ መንግሥትና ፡ የሱዳን ፡ ሕዝብ ፡
ያቀረበውን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንዳቀ
ርብ ፡ በትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

❋ ❋ ❋

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የሱዳን ፡ መንግሥት ፡ የመጀመሪ
ያው ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆነው ፡
የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የተሾሙበትን ፡
ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

ከክቡርነትዎ ፡ ንግግር ፡ እንደሰማነው ፡ በታላቁ ፡ በግርማዊ ፡ አጼ ፡
ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የሱዳን ፡ መልክተኛ ፡ ሁነው ፡ ከመጡት ፡
ከታላቁ ፡ ሐጂ ፡ ካሌድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚወለዱ ፡ መሆንዎን ፡ በማወ

ቃችን ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህም ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ ዕድልዎ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ መካከል ፡ ለሚኖረው ፡ ጉዳይ ፡ መቃናት ፡ መልካም ፡ ምልክት ፡ ነው ።

በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ታሪካዊ ፡ ወዳጅነት ፡ በሁለቱ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘው ፡ መልካም ፡ ግንኙነት ፡ በሁለቱም ፡ መንግሥቶቻችን ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የኀብረት ፡ መረዳዳት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲታሰብ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መተሳሰሪያ ፡ በየጊዜው ፡ እየጠነከረና ፡ እየተስፋፋ ፡ እንደሚሄድ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ክቡርነትዎ ፡ የተላኩበትን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ የዘወትር ፡ ሐሳባችንና ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እርዳታ ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ።

ለተከበሩት ፡ የሱዳን ፡ ሪፑብሊክ ፡ ከፍተኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ሰላምታችንና ፡ መልካም ፡ ምኞታችንን ፡ እንዲያቀርቡልን ፡ እንደዚሁም ፡ በእነርሱ ፡ አማካይነት ፡ ለመላው ፡ የሱዳን ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምታችን ፡ እንዲደርስ ፡ እንዲያደርጉልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 572

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሕንድን ፡ ለመጐብኘት ፡ ስለሚሄዱ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚኖሩት ፡ ሕንዳዊያን ፡ ጥቅምት ፡ ፩ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ ማኅበር ፡ አዳራሽ ፡ የመሰናበቻ ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ አስደሳች ፡ ጨዋታ ፡ ባሳዩበት ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ከተመለከቱላቸው ፡ በኋላ ፡ የሕንድ ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ናራንጃን ፡ ሲንግልና ፡ የሕንድ ፡ ኮሙኒቲ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ።

ሀ) የክቡር ፡ ናራንጃን ፡ ሲንግል ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ የክብር ፡ እንግዳ ፡ በመሆን ፡ በትሕትና ፡ እዚህ ፡ በመገኘተዎ ፡ በራሴና ፡ እንዲሁም ፡ እዚህ ፡ ባሉት ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆች ፡ ስም ፡ ምስጋናዬን ፡ ሳቀርብ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ፡ ወደ ፡ ሕንድ ፡ ለኦፊሴል ፡ ጉብኝት ፡ በቅርቡ ፡ ከመሄድዎ ፡ በፊት ፡ በዚሁ ፡ ሥራ ፡ በሚበዛብዎ ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ በመገኘትዎ ፡ በተለይ ፡ ሁላችንም ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን።



ይኸውም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ባገራችንና ፡ በምሥራቅ ፡ የሚፈጽሙት ፡ ታላቅ ፡ ጉብኝታዊ ፡ ጉዞ ፡ ሲሆን ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ የምንገኝ ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆች የግርማዊነትዎን ፡ መልካም ፡ አገዛዝ ፡ በጣም ፡ የምናመሰግን ፡ ከመሆናችንም ፡ በላይ ፡ ይህንኑ ፡ ስንጠባበቅ ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ አልፎአል ።

ግርማዊነትዎ ፡ በሥልጣኔዋ ፡ እንደ ፡ ሕንድ ፡ ጥንታዊ ፡ የሆነች ፡ አገር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጀግና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ መላሽ ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጠው ፡ መሪ ፡ ሕዝቡን ፡ በመምራት ፡ ልማድና ፡ ስም ፡ ያለዎ፡ መሆኑና ፡ የዓለም ፡ ሰላምና ፡ እድገት ፡ እንዲጐለምስ ፡ ያለጥርጥር ፡ የሚደግፉ ፡ መሆንዎ ፡ ጭምር ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ታውቆአል ።

ግርማዊነትዎ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕንድ ፡ የተመሳሰለ ፡ ሁኔታዎች ፡ ያሏቸው ፡ መሆናቸውን ፡ በአየሩ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በሚገኙት ፡ የአገር ፡ ውበቶች ፡ በእንስሳቱና ፡ በዕፅዋቱ ፡ ለእንግዳ ፡ በሚደረገው ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ አቀባበል ፡ በጉብኝቱ ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ የሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ ጉዳዮች ፡ (ፕሮግራሞች) በጣም ፡ የተመሳሰሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ጭምር ፡ እዚያው ፡ ያውቁታል ።

እነዚህ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳዮች ፡ እዚህ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መሪነት ፡ በታላቅ ፡ ትጋት ፡ እንደሚፈጽሙ ፡ ሁሉ ፡ እዚያም ፡ እንዲሁ ፡ በመከናወን ፡ ላይ፡ ይገኛሉ ። የሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ያለው ፡ አድናቆትና ፡ ናፍቆት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ በጉብኝትዎ ፡ ወራት ፡ እንደንግዳ ፡ የሚመለከትዎ ፡ አይገኝም ።

ይህ ፡ ጉዞ ፡ መልካም ፡ እንዲሆንልዎና ፡ እንዲሁም ፡ በተለይ ፡ የሕንድ ፡ ጉብኝትዎ ፡ ደስታ ፡ የመላበት ፡ እንዲሆንልዎ ፡ እንመኛለን ።

* * *

ለ) የሕንዱ ፡ ኮሙኒቲ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ንግግር ።

## ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ፡ ማታ ፡ በመካከላችን ፡ በመገኘትዎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሚገኙት ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆችና ፡ በራሴም ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምስጋና ፡ በትሕትና ፡

አቀርባለሁ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሕንድን ፡ አገር ፡ በኦፊሲዬል ፡ ለመጐብኘት ፡ ከመነሳትዎ ፡ አስቀድሞ ፡ እጅግ ፡ የተከበረውን ፡ የሥራ ፡ ጊዜዎን ፡ በመሠዋት፡ በመካከላችን ፡ ለመገኘት ፡ ዕድል ፡ ስለሰጡን ፡ ደስታችን ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ለመናገር ፡ ይፈቀድልኝ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የሚያደርጉት ፡ የምሥራቅ ፡ ጉዞ ፡ ታላቅ ፡ ሲሆንና ፡ አገራችንን ፡ ሲጐበኙልን ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በግርማዊነትዎ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እጅግ ፡ ተደስተን ፡ በሰላም ፡ የምንኖረው ፡ ውለታዎን ፡ መቼውንም ፡ የማንዘነጋው ፡ እኛ ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆች ፡ ግርማዊነትዎ ፡ አገራችንን ፡ የሚጐበኝበትን ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ናፍቆት ፡ ስንጠባበቅ ፡ ቆይተናል ።

እንደ ፡ ሕንድ ፡ በጥንታዊ ፡ ሥልጣኔዋ ፡ በታወቀች ፡ አገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትዎ ፡ አገሪቱን ፡ በቆራጥ ፡ ጀግንነት ፡ ነፃ ፡ በማውጣትዎ ፡ የተወደደች ፡ አገርዎን ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ለማልማት ፡ የፈጸሙት ፡ የታሪክ ፡ ሰውነትዎ ፡ እንደዚሁም ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሰላምና ፡ መግባባት ፡ የፈጸሙት ፡ ተጋድሎ ፡ ወደ ፡ እናት ፡ አገራችን ፡ ከመድረስዎ ፡ አስቀድሞ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ ሕንድን ፡ በሚጐበኝበት ፡ ወቅት ፡ ከተወደደችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ በአገር ፡ አቀማመጥ ፡ በተክልና ፡ በዓየር ፡ እንደዚሁም ፡ የእንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡ ባሕል ፡ እንደሚገጥምዎ ፡ አንጠራጠርም ።

በሕንድ ፡ ምድር ፡ የኢትዮጵያን ፡ የመሰለ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ ባሕል ፡ እንደመኖሩ ፡ መጠን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አርቆ ፡ ተመልካችነትና ፡ ብልህ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደተጀመረው ፡ እርምጃ ፡ መንግሥቱ ፡ የሕዝብን ፡ ኑሮ ፡ ለማሻሻል ፡ ይጣጣራል ።

ግርማዊነትዎ ፡ በሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሲገኙ ፡ እንግዳ ፡ አይሆኑበትም ።

የግርማዊነትዎ ፡ የታሪክ ፡ ሰውነትና ፡ የፈጸሙት ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡



በሕዝቡ ፡ ልብ ፡ የአድናቆትና ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ ቀርጾአል ።

ግርማዊነትዎ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በሚያደርጉት ፡ ታሪካዊ ፡ ጉዞ ፡ በወዳጅ ፡ አገር ፡ ሕንድ ፡ ምድር ፡ በሚቆዩበት ፡ ጊዜያት ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖልዎት ፡ እንደተወዳጅ ፡ አገርዎ ፡ ያህል ፡ ስሜት ፡ እንዲያገኙ ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡<br>
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡<br>
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ ትኑር ።

✻ ✻ ✻

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ሕንድን ፡ ለመጐብኘት ፡ ከመሄዳችን ፡ በፊት ፡ ከዚህ ፡ መገኘታችንን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ ለገለጹልን ፡ መልካም ፡ ቃሎች ፡ ስንመልስልዎ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

እናንተ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የምትገኙ ፡ የሕንድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ የሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ እንደምታውቁት ፡ ታላቂን ፡ አገራችሁን ፡ ለመጐብኘት ፡ ክቡር ፡ ፕሬዚዳንታችሁን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትራችሁንና ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቻችሁን ፡ ለመገናኘት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያሰብነውና ፡ የምንጠባበቀው ፡ ነገር ፡ ነው ።

በአምባሳደራችሁ ፡ አማካይነትና ፡ አሳሳቢነት ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ እንድንጐበኝ ፡ አስፈላጊው ፡ ድርጅት ፡ ተደርጓል ። በምዕራብ ፡ በደቡብ ፡ በሰሜንና ፡ በምሥራቅ ፡ ሕንድ ፡ የሚገኙትን ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞቻችሁን ፡ ለመጐብኘት ፡ መንደሮቻችሁንና ፡ ፋብሪካዎቻችሁን ፡ የመሐንዲስና ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችሁን ፡ ለማየት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከሕንድ ፡ ሕዝብ ፡ የተቻለንን ፡ ያህል ፡ ከታላቁም ፡ ከትንሹም ፡ ለመገናኘት ፡ ምኞታችንና ፡ ሐሳባችን ፡ ነው ። ብዙ ፡ የምናየውና ፡ ብዙ ፡ የምንማረው ፡ ነገር ፡ እንደሚኖር ፡ እርግጥ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኙ ፡ በሕንድ ፡ ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ የምናውቀውን ፡ መልካም ፡ አቀባበልና ፡ አስተያየት ፡ በሕንድ ፡ አገር ፡ እንደምናገኝ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ይኸን ፡ በዓል ፡ ያዘጋጀውን ፡ ማኅበር ፡ ይኸን፡ ደስ ፡ ያሰኘንን ፡ ጨዋታ ፡ ያሳየንን ፡ ሕፃናት ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

# 573

የዩጎስላብ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፌደራል ፡ ፓፒሌር ፡ መንግሥት ፡ አምባሳደር ፡ ሚስተር ፡ ማንጃን ፡ ባሪሺች ፡ ጥቅምት ፡ ፪ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ. ም በ፫ ሰዓት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ አምባሳደሩ ፡ ንግግር ።

የዩጎስላብ ፡ ፌዴሬቲቭ ፡ ፓፑሌር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ማርሻል ፡ ብሮዝ ፡ ቲቶ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሆኜ ፡ እንድሠራ ፡ የሾሙበትንና ፡ እንዲሁም ከኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ድሻን ፡ ክቬደር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤዎች ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ የሚሰማኝ ፡ ክብር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

የግርማዊነትዎ ፡ ዩጎዝላቭን ፡ መጐብኘትና ፡ የፕሬዚዳንት ፡ ዦዜፕ ፡ ብሮዝ ቲቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ መጐብኘት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያስገኘው ፡የጋራ ፡ ግኑኙነቶች ፡ እንዳከናውን ፡ የተጣለብኝን ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ከሕሊናዬ ፡ ውስጥ ፡ መሥርቼዋለሁ ።

እነዚህም ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ጉብኝቶች ፡ በሁለታችን ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጸንተው ፡ የቆዩትን ፡ የወዳጅ ፡ ግንኙነት ፡ ማጠንከር ፡ ብቻ ሳይሆን ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ሰላም ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጋራ ፡ መሥዋዕትነትን ፡ አድርገዋል ።

ባለፉት ፡ ጊዜያቶች ፡ ለነፃነታችን ፡ የአደረግነው ፡ የጋራ ፡ ትግል ፡ ወራሪዎችን ፡ በመቃወም ፡ ሁለቱ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ ያደረጉት ፡ ጥንካሬና ፡ እንዲሁም ፡ ሰላም ፡ ፈላጊዎች ፡ በመሆናችን ፡ በመንግሥቶቻችን ፡ መካከል ፡ የሚነሱት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ እንዲያልቁ ፡ ለማድረግ ፡ ያሉን ፡ ተመሳሳይ ፡ ዓላማዎች ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ መተሳሰርን ፡ ሊመሠርቱ ፡ ችለዋል ።

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ፀንቶ ፡ የቆየውን ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ በሰፊው፡ ለማከናወን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እንደሆነ ፡ ስለተረዳሁ ፡ ሥራየን ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነትዎና ፡ የመንግሥትዎ፡ እርዳታ ፡ እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በጎ ፡ አድራጐትዎ ፡ እንዳይለየኝ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እለምናለሁ ።



ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መልካም ፡ ጸጋ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ክብርና ፡ ልማት ፡ ካለው ፡ ምኞት ፡ ጋር ፡ ፕሬዝዴንት ፡ ዦዜፕ ፡ ብሮዝ ፡ ቲቶ ፡ የላኩትን ፡ የወዳጅ ፡ ሰላምታ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ደስታዬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ አምባሳደር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የዩጎስላቭያ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሁነው ፡ ከዩጎስላቭ ፡ ፌደራል ፡ ሕዝባዊ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሰጠዎትን ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

እንደዚሁም ፡ ከእርስዎ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ዱሻን ፡ ክቬደር ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ስንቀበል ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መግባባትና ፡ መተባበር ፡ እየጸናና ፡ እየተስፋፋ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ የፈጸሙትን ፡ አገልግሎት ፡ ሳናስታውሰው ፡ አናልፍም ።

ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለፕሬዚዳንት ፡ ቲቶ፡ ሰላምታችንንና ፡ ስለራሳቸውም ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲያቀርቡልን ፡ እንደዚሁም ፡ እኛ ፡ በዩጎስላቭ ፡ ያደረግነውን ፡ መጎብኘት ፡ ማርሻል ፡ ቲቶን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያደረጉትን ፡ መጎብኘት ፡ በደስታ ፡ የምናስታውሰው ፡ መሆናችንን ፡ ለማርሻል ፡ እንዲገልጹላቸው ፡ እንጠይቅዎታለን።

ክቡርነትዎ ፡ የተላኩበትን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ለሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ የዘወትር ፡ አሳባችንና ፡ እንዲሁም ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እርዳታና ፡ መተባበር ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ። የመጡበትን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያደርጉት ፡ ድካም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በዩጎስላቭያ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነትና ፡ የጋራ ፡ መግባባት ፡ በበለጠ ፡ እያጠነከረውና ፡ እያስፋፋው ፡ እንደሚሄድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።